በኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት
የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን

# የ 1987 አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ መመሪያ

ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚገኙ መረጃዎች ሥነ-ሕዝብን በተመለከተ ለሚወጡ ፖሊሲዎች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ!

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት የመኖሪያ ቤቶችን በተመለከተ ለሚቀየሱ ዕቅዶች ዝግጅት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል !

ቆጠራው ወንድን፣ሴትን፣ ሕጻናትን፣ አዛውንትን በሙሉ ይመለከታል !

ሁሉም ራሱን ቤተሰቡንና ቤቱን ያስቆጥር !

አዲስ አበባ
ነሐሴ 1986 ዓ.ም.

በኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት
የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን

# የ 1987 አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ መመሪያ




ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚገኙ መረጃዎች ሥነ-ሕዝብን በተመለከተ ለሚወጡ ፖሊሲዎች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ!

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት የመኖሪያ ቤቶችን በተመለከተ ለሚቀየሱ ዕቅዶች ዝግጅት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል !

ቆጠራው ወንድን፣ሴትን፣ ሕጻናትን፣ አዛውንትን በሙሉ ይመለከታል !

ሁሉም ራሱን ቤተሰቡንና ቤቱን ያስቆጥር !

አዲስ አበባ
ነሐሴ 1986 ዓ.ም.

# ማውጫ


| ክፍል | አርዕስት | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | መግቢያ ........................................ | 1 |
| 2. | የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ዓላማዎች ........................ | 1 |
| 3. | የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ የሚካሄድባቸው ዘዴዎች ................................ | 2 |
| | 3.1 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ አፈጻጸም ሁኔታ ............ | 2 |
| | 3.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ የሚያካሂዱ አካላት ............................ | 3 |
| 4. | የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትርጉም ዓላማና ጥቅም ........................ | 3 |
| | 4.1 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትርጉም ........................ | 3 |
| | 4.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዓላማዎች ........................ | 3 |
| | 4.3 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚሰጠው ጥቅሞች ........................ | 4 |
| | 4.4 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሲካሄድ መሟላት ያለባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች............................ | 6 |
| 5. | የሕዝብና ቤት ቆጠራ በኢትዮጵያ ............................ | 6 |
| 6. | የ 1987 አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ........................ | 8 |
| | 6.1 የቆጠራው አስፈላጊነት ........................ | 8 |
| | 6.2 የሚሸፍነው አካባቢ ........................ | 8 |
| | 6.3 የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ........................ | 8 |
| | 6.4 የሠራተኞች ምልመላ፣ ሥልጠናና ሥምሪት ........................ | 8 |
| | 6.5 ቆጠራው የሚወስደዉ ጊዜ........................ | 9 |
| | 6.6 በቆጠራው የሚሰበሰቡት መረጃዎች ዓይነት ትርጉምና ጽንሰ ሃሳብ ........................ | 9 |
| 7. | የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈጸሚያ አዋጅና የግለሰቦችና ድርጅቶች ኃላፊነትና ግዴታ ........................ | 23 |
| | 7.1 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈጸሚያ አዋጅ ........................ | 23 |
| | 7.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ በሚከናወንበት ወቅት ግለሰቦችና ድርጅቶች ስለሚኖራቸው ኃላፊነትና ግዴታ ........................ | 24 |
| 8. | የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ድርጅታዊ መዋቅር ተግባርና ኃላፊነት ............ | 24 |
| | 8.1 የማዕከላዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር ............ | 25 |
| | 8.2 ከማዕከላዊ ኮሚሽን በታች እስከ ወረዳ የሚገኙ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽኖች ሥልጣንና ተግባር ........................ | 26 |
| 9. | የሕዝብና ቤት ቆጠራ የመስክ ሥራ ሂደት ........................ | 26 |

# 1. <u>መግቢያ</u>

የአንድን አገር ሕዝብ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን የሚያንፀባርቁ አጠቃላይ መረጃዎች የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና ከፍ ለማድረግ ለሚቀየሱ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ልማት ዕቅድ ለማዘጋጀት፣ እንዲሁም በተግባር ላይ የሚለዉን የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ልማት ዕቅድ ያስገኘዉን ዉጤት ለመገምገም፣ ለመከታተልና የተለያዩ ጥናቶችንም ለማካሄድ መሠረት በመሆን ያገለግላሉ። እነዚህ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ሁኔታን የሚያንፀባርቁ አጠቃላይ መረጃዎች የሚባሉት እንደ ሕዝብ ብዛት፣ ልደት፣ ሞት፣ ፍልሰት፣ የቤቶች ብዛትና ሁኔታ፣ የጤና፣ የትምህርትና የሥራ ሁኔታ፣ የእርሻ፣ የንግድ፣ የትራንስፖርትና መገናኛ ... ወዘተ. ያሉ መረጃዎች ሲሆኑ አብዛኛዉን ጊዜ መረጃዎቹ የሚገኙት፣

- ሀ/ ጠቅላላ ቆጠራ (census) በማካሄድ፣
- ለ/ የናሙና ወይም ከፊል ቆጠራ (sample survey) በማካሄድ፣
- ሐ/ የማያቋርጥ የልደት፣ የሞትና የፍልሰት ምዝገባ (Vital Statistics Registration) በማካሄድና፣
- መ/ ከአስተዳደር መዛግብቶች (Administrative Records) ነዉ።

ሕዝብና ቤትን የሚመለከቱ መረጃዎች ከላይ የተጠቀሱትን አራቱን ዘዴዎች መሠረት በማድረግ ሊገኙ የሚችሉ ሲሆን፣ የእነዚህ መረጃዎች አብይ ምንጭ ግን ሕዝብና ቤትን በተመለከተ አጠቃላይ ቆጠራ በማካሄድ የሚገኙ መረጃዎች ናቸዉ።

በሕዝብና ቤት ቆጠራ የተሟላ መረጃ ለማግኘት ቆጠራው በታቀደው መሠረት መከናወን ያለበት ከመሆኑም በላይ የሚመለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ትክክለኛ መረጃ በመስጠት ረገድ ትብብር ማድረግ ይኖርባቸዋል። እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈልገው ትክክለኛ ባልሆነ ወይም በተሳሳተ መረጃ ላይ በመመሥረት የሚዘጋጅ የልማት ዕቅድም ሆነ የሚወሰድ የፖሊሲ እርምጃ ወደሚፈለገው ግብ የማያደርስ ከመሆኑም በላይ አስፈላጊ ያልሆነ የጊዜ፣ የገንዘብ የንብረትና የጉልበት መባከን የሚያስከትል ስለመሆኑ ነው።

የ1987 አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ አፈጻጸም የተሳካ እንዲሆን የመንግሥታዊና የሕዝባዊ ድርጅቶችን እንዲሁም የሕዝቡን የነቃ ተሳትፎና ድጋፍ ስለማስፈለጉ አጠያያቂ አይሆንም። በዚህ አኳያ ቆጠራው ከመካሄዱ በፊት ስለ ቆጠራው አስፈላጊነትና ጠቃሚነት በማሳወቅ ኅብረተሰቡ ለቆጠራው ያለውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ቆጠራው የሚጠይቀውን ሁሉ አሟልቶ እንዲገኝ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህን ተግባር ለማከናወን የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራን በወቅቱ ማካሄድ ያስፈልጋል።

ስለሆነም የትምህርትና ቅስቀሳውን ሥራ በሁሉም አካባቢ በተመሳሳይ ሁኔታ ለማከናወን እንዲቻል ይህ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ መመሪያ መሠረት ሆኖ እንዲያገለግል ተዘጋጅቷል። በዚህ መመሪያ ውስጥ ስለ ሕዝብና ቤት ቆጠራ ትምህርትና ቅስቀሳ ዓላማዎች፣ ስለሕዝብና ቤት ቆጠራ፣ ትርጉም፣ ዓላማና ጥቅም፣ ቆጠራውን ለማካሄድ መሟላት ስላለባቸው ጉዳዮች፣ በቆጠራው ስለሚሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነት ትርጉም፣ ጽንሰ ሀሳብ፣ ቆጠራው በሚከናወንበት ወቅት ግለሰቦችና ድርጅቶች ስለሚኖራቸው ኃላፊነትና ግዴታ ... ወዘተ በተቻለ መጠን ተብራርቷል። እንደሁኔታውና እንደ አካባቢው እየታየ ይህን መመሪያ መሠረት በማድረግ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ መካሄድ ይኖርበታል።

# 2. <u>የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ዓላማዎች</u>

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ በጣም ግዙፍ፣ በርካታ የገንዘብ ወጪና ብዙ የሰዉ ኃይል የሚያስፈልገዉ በመሆኑ የአንድ መ/ቤት ወይም ድርጅት ብቻ ኃላፊነት ሊሆን አይችልም። ከቆጠራ የሚገኙት ዉጤቶች በመንግሥትና በሌሎች የቆጠራ ዉጤት ተጠቃሚዎች ዘንድ ተፈላጊነታቸዉ ከፍ እያለ መጥቷል። በአንጻሩ ደግሞ በቆጠራዉ የሚጠየቁ ግላዊ የማህበራዊና የኢኮኖሚ መረጃዎች ህብረተሰቡ ለቆጠራዉ እንዲኖረዉ የሚያስፈልገዉን ከፍተኛ ግንዛቤ ከሚገመተዉ በላይ እያሳደጉት መጥተዋል። እነዚህ መረጃዎች ሲሰበሰቡ ከህብረተሰቡ ከፍተኛ ትብብርና ድጋፍ ማግኘት ያስፈልጋል። የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ግብ መምታት በአብዛኛዉ የሚወሰነዉ የቆጠራዉ ሥራ ጠቃሚነት በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ሲኖረዉና ህብረተሰቡ ለሥራዉ በከፍተኛ ደረጃ ሲተባበር ነዉ። በመሆኑም በሕዝቡ ዘንድ የቆጠራዉ ጠቀሜታ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማድረግ ቆጠራዉን አስመልክቶ ጥልቀትና ስፋት ያለዉ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ማካሄድ አማራጭ የሌለዉ ነዉ።

የቆጠራዉ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ህብረተሰቡን ስለቆጠራዉ ጥቅም ማሳመን መቻል ያለበት ሲሆን ይህም ሊፈጸም የሚችለዉ ህብረተሰቡን በሕዝብና ቤት ቆጠራ መጠይቆች ዉስጥ የተካተቱን ጥያቄዎች እንዴት መመለስ እንዳለባቸዉ የሚሰበሰቡት መረጃዎች በምን ጥቅም ላይ እንደሚዉሉ በማስተማርና በማሳወቅ ሊኖር የሚችለዉን ጥርጣሬ የማስወገድ አቅም ሲኖረዉ ነዉ። የቆጠራው ሥራ የተሳካ እንዲሆንና ብሎም የተሟላ፣ ትክክለኛና አስተማማኝ መረጃዎች ከሚመለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ለማግኘት እንዲቻል የቆጠራው የመስክ ሥራ ከመጀመሩ በፊትም ሆነ ቆጠራው በመካሄድ ላይ እያለ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ማካሄድ ያስፈልጋል። የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ቀደምተኛ ዓላማ ለቆጠራው አፈጻጸም መሳካት የሕዝቡን ሙሉ ትብብር ከፍተኛ ድጋፍና ተሳትፎ ለማግኘት ቆጠራው ከመካሄዱ በፊት ስለቆጠራው ምንነት፣ አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ለማሳወቅ ሲሆን ዝርዝርና ዋና ዋና ዓላማዎቹ የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. ሊካሄድ ስለታቀደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ምንነት በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲሁም በሕዝብ ዘንድ እንዲታወቅ ለማድረግ፣

ለ. ስለ ቆጠራው ጠቃሚነትና አስፈላጊነት ለሕዝብ ለማሳወቅ፣

ሐ. ከቆጠራው የሚገኙ መረጃዎችን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት በመረዳት ቆጠራው በሚካሄድበት ወቅት የሚመለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ትክክለኛውን መረጃ በመስጠት ያልተቆጠበ ድጋፍና ትብብር ለቆጣሪዎች ማድረግ ያለባቸው መሆኑን ለማሳወቅ።

## 3. የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ የሚካሄድባቸው ዘዴዎች

የቆጠራው የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ሊካሄድ ከሚችልባቸዉ ዘዴዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሕዝብ መገናኛና የመድረክ ላይ ቅስቀሳ ናቸው። እነዚህ ዘዴዎች ስለቆጠራው ለማስተላለፍ የሚፈለጉትን መልክቶች ለሕብረተሰቡ በማድረስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ይገመታል።

### ሀ. በሕዝብ መገናኛ የሚከናወነው የትምህርትና የቅስቀሳ ሥራ

በሬዲዮና በቴሌቪዥን ስለቆጠራው ቃለ መጠይቆችንና ማብራሪያዎችን ማስተላለፍ፣ አጫጭር የሆኑ የቆጠራ ማስታወቂያዎችንና ድራማ መሰል ዝግጅቶችን ከተቻለም በመዝሙር መልክ ማቅረብ። በተጨማሪም በመንግሥትና በግል ጋዜጦችና መጽሄቶች ስለ ቆጠራው አጫጭር ጽሁፎችንና ካርቱኖችን ማዘጋጀት። እንዲሁም በተለያዩ የሕዝብ መዝናኛ ቦታዎች በሚታይ መልኩ የሚለጠፉ/የሚንጠለጠሉ መፈክሮችንና ፖስቶሮችን፣ በሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች የሚሠራጩ በራሪ ጽሁፎችን መበተንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

### ለ. የመድረክ ላይ ቅስቀሳ ሥራ

ይህም በሴሚናሮች፣ በስብሰባዎችና ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ማለት አብያተ ክርስቲያናት ገዳማት መስጊዶች ትምህርት ቤቶች ፊልምና ትያትር ቤቶች... ወዘተ. ስለሕዝብና ቤት ቆጠራ አጠቃላይ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች መሥጠትን ያጠቃልላል።

### 3.1 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ አፈጻጸም ሁኔታ፣

የትምህርትና የቅስቀሳው ሥራ በተለያዩ ደረጃዎች እንዲካሄድ ይደረጋል።

ሀ. በተለያዩ የሕዝብ መገናኛዎች መግለጫ መስጠት፣

ለ. ከብሄራዊ ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ የቆጠራውን ሥራ ማስተባበርና የመምራት ኃላፊነት ለሚሰጣቸው ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎችና ለሕዝባዊ ድርጅቶች መሪዎች ሴሚናር ማካሄድ፣

ሐ. ቆጠራውን በሚመለከት በየደረጃው በሚሰጠው ሴሚናር በተሳተፉ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሕዝባዊ ድርጅቶች አማካኝነት ለኅብረተሰቡ የቆጠራውን ትምህርትና ቅስቀሳ ማስተላለፍ።

ከላይ በተጠቀሱት ሴሚናሮችም ሆነ ስብሰባዎች ቅስቀሳው ሲካሄድ በሁለት ዙር ቢሆን ይመረጣል። ይኸውም በመጀመሪያው ዙር ማለትም ቆጠራው ከመጀመሩ ትንሽ ቀደም ብሎ ስለ ቆጠራው ዓላማና ጥቅም በቆጠራው ስለሚሰበሰቡ መረጃዎች፣ መረጃዎቹ በሚስጥር የሚጠበቁ ስለመሆኑ ማሳወቅ። እንዲሁም በሁለተኛው ዙር ማለትም ቆጠራው ሲጀመር በቆጠራው ስለሚሰበሰቡት መረጃዎች ዝርዝር፣ ስለ መጠይቁ አሞላል እንዲሁም እያንዳንዱ ግለሰብ ሳይቆጠር እንዳይቀር ወይም በድጋሚ እንዳይቆጠር ማብራራትና ማሳወቅ ናቸው።

3.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ የሚያካሄዱ አካላት፣

የቆጠራውን የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ለማከናወን የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይጠበቃል። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የማስታወቂያ ሚኒስቴር፣
ለ. ቆጠራውን በየደረጃው የሚመሩና የሚያስተባብሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ኃላፊዎችና የሕዝባዊ ድርጅቶች መሪዎች፣
ሐ. በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን መዋቅር ውስጥ በትምህርትና ቅስቀሳ ዘርፍ የተመደቡ ሠራተኞች፣
መ. በሕዝባዊ ድርጅቶች /የገበሬና የቀበሌ ማኅበራት፣ . . . ወዘተ./፣
ሠ. የቆጠራውን የመስክ ሥራ በሚያከናውኑ ሠራተኞች /ተቆጣጣሪዎችና ቆጣሪዎች/፣
ረ. በትምህርት ቤቶች /አስተማሪዎችና ተማሪዎች/፣
ሰ. በኃይማኖት መሪዎች።

ከጥቅምት 1ቀን 1987 ጀምሮ ሊካሄድ የታቀደዉን የሕዝብና ቤት ቆጠራ በተሳካ ሁኔታ ለማስፈጸም የሚካሄደዉ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ ይህን መመሪያ መሠረት በማድረግ የሚፈጸም ቢሆንም ቅስቀሳውን የሚያካሄዱ አካላት ቅስቀሳው የሚካሄድበትን አካባቢ፣ ህብረተሰብ ወይም የሴሚናርና የስብሰባ ተካፋዮችን ግንዛቤ ከግምት ውስጥ በማስገባት የራሳቸውን የአቀሳቀስ ስልት በመቀየስ ቅስቀሳውን ማካሄድ ይኖርባቸዋል።

## 4. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትርጉም ዓላማና ጥቅም

### 4.1 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ትርጉም

የሕዝብና ቤት ቆጠራ አጠር ባለ ሁኔታ ሲገለጽ በተወሰነ ወቅትና በአገር አቀፍ ደረጃ ወይም በአገር ውስጥ በተወሰነ የአስተዳደር ክልል ስለአለው ሕዝብና ስለሚገኙት ቤቶች ብዛት፣ ስለ ሕዝቡ የዲሞግራፊ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ባሕሪያት እንዲሁም ስለቤቶች ሁኔታ የሚገልጹ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀርና ከዚያም አስተማማኝነቱንና ትክክለኛነቱን በመገምገም የተገኘውን ውጤት ለተጠቃሚዎች የማሠራጨት ተግባራትን ያጠቃልላል።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት ከአነስተኛ የአስተዳደር ክልል ማለትም ከገበሬ ማህበር ወይም ከቀበሌ ማህበር ጀምሮ እስከ ብሄራዊ ክልል ከዚያም በሀገር አቀፍ ደረጃ በገጠርና በከተማ መረጃዎችን ያስገኛል።

### 4.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዓላማዎች

የመጀመሪያዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከተካሄደ አሥር ዓመታት ተቆጥረዋል። በእነኚህ ዓመታት ዉስጥም በርካታ ሁኔታዎች ተከስተዋል። በቆጠራዉ ማግስት የነበረዉ ረሃብ፣ የመንደር ምሥረታ ፕሮግራም፣ ከ1983 ዓ.ም. በፊት የነበረዉ ጦርነት፣ ከ1983 ወዲህ ያለዉ በርካታ የፖሊሲ ለዉጥ ወዘተ. ከቆጠራዉ ጀምሮ ከተካሄዱት አበይት ክንዉኖች መካከል ዋነኞቹ ናቸዉ። የእነዚህ ክንዉኖች በስነ ሕዝብ መረጃዎች ላይ የሚያስከትለዉ ተጽዕኖ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም። በመሆኑም በነዚህ ለዉጦች ሳቢያ በ1976 በተካሄደዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተሰበሰበዉ መረጃ የወቅቱን ሁኔታ ያሳያል ብሎ መገመት በጣም አስቸጋሪና አሳሳችም ይሆናል። ስለሆነም የአገሪቱን ሕዝብና ቤቶች በሚመለከት ለሚኒሱ መሠረታዊ የመረጃዎች ጥያቄ የተሟላ፣ አስተማማኝና ወቅታዊ መልስ ለመስጠት እንዲቻል በብሄራዊ ደረጃ ለሁለተኛ ጊዜ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መካሄድ ይኖርበታል። በዚህ መሠረት የሚካሄደዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ።

ሀ. <u>የሕዝብ ብዛት መረጃዎችን ማስገኘት፣</u> የቆጠራዉ ዉጤት ወቅታዊና አስተማማኝ የሆኑ የሕዝብ ብዛትን በዕድሜና በጾታ የሚያመለክቱ መረጃዎችን በገጠርና በከተማ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና እንዲሁም በዝቅተኛ ደረጃ ለሚገኙ የአስተዳደር ክፍሎች/ገበሬ ማህበር፣ ቀበሌ ማህበር፣ ... ወዘተ./ ለማግኘት፣

ለ. <u>ስለ ሕዝቡ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ባሕርያትን የሚያመለክቱ መረጃዎችን ማስገኘት፣</u> ስለ ሕዝቡ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ባሕርያት እንደ ብሄረሰብ፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ዓይነት፣ ...ወዘተ መረጃዎችን ለማግኘት፣

ሐ. <u>ስለ ሕዝቡ የዲሞግራፊ ባሕርያትን የሚያመለክቱ መረጃዎችን ለማግኘት፣</u> የሕዝቡን የየዓመቱን ብዛት ዕድገት ለማስላትና እንዲሁም የሕዝቡን ብዛት በተመለከተ የወደፊት /ለመጪዉ አምስት፣ አሥር ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ዓመታት/ የሕዝብ ብዛት ትንበያ ለማዘጋጀት የሚረዱ እንደ ልደት፣ ሞትና ፍልሰት መጠን የሚያሳዩ መረጃዎችን ለማግኘት፣

መ. <u>ቤቶችን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት፣</u> የቆጠራዉ ዉጤት ወቅታዊና አስተማማኝ የሆነ የቤቶችን ብዛትና ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎች በገጠር፣ በከተማ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና እንዲሁም በዝቅተኛ ደረጃ ለሚገኙ የአስተዳደር ክፍሎች መረጃዎች ለማግኘት፣

ሠ. <u>ለሕዝባዊ ምርጫ ማስፈጸሚያ የሚረዱ መረጃዎችን ለማግኘት፣</u> ለሕዝባዊ ምርጫ ማስፈጸሚያ የሚረዱትን ማለትም የምርጫ ክልሎችን ለመወሰንና ለመለየት የሚጠቅመዉን የሕዝብ ብዛት በዝቅተኛ አስተዳደር ክፍሎች እንዲሁም የመራጮችንና የተመራጮችን ብዛት የሚያመለክቱ መረጃዎችን ለማግኘት ናቸዉ።

## 4.3 <u>የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚሰጠው ጥቅሞች</u>

የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚሰጠው አበይት ጥቅሞች የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. <u>ሕዝቡን በተመለከተ መሠረታዊና ዝርዝር መረጃዎችን ለማግኘት ይጠቅማል</u>

ቆጠራው የሕዝቡን ብዛት በጾታና በዕድሜ፣ በገጠርና በከተማ፣ በወረዳ፣ በዞን፣ በብሄራዊ ክልላዊ መስተዳድርና እንዲሁም በሀገር ደረጃ መረጃዎች ያስገኛል። እንዲሁም የሕዝቡን ሌሎች ባሕሪያት የሚያመለክቱ ማለትም ብሄረሰብ፣ ቋንቋ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የሥራ ዓይነት፣ ልደት፣ ሞት፣ ፍልሰት፣ ...ወዘተ. መረጃዎችን በየአስተዳደር ደረጃ ለማግኘት ቆጠራው ይጠቅማል።

ለ. <u>ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲና ዕቅድ ዝግጅትና ክትትል ይጠቅማል</u>

ከሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ የሚገኙት መረጃዎች ስለሕዝቡ ብዛትና ሥርጭት እንዲሁም ስለተለያዩ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ባሕርያቱን ማወቅ በወቅቱ ያለውን የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና ሌሎች ባሕሪያት ሁኔታ ለመገምገም ብቁ ስለሚያደርግ በተደረገው ግምገማ መሠረት የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ይበልጥ ለማሻሻል የሚያስችሉ አግባብ ያላቸውን ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች ለመንደፍ ያስችላል። ይበልጡንም ደግሞ የአገሪቱን ወይም የክልሉን ሕዝብ ብዛት፣ አሰፋፈርና ሥርጭት በማወቅ፣ በትምህርት፣ ሥራ በመፍጠር፣ የሰው ኃይል በማደራጀት፣ በቤተሰብ ምጣኔ፣ በጤና፣ በቤት አቅርቦት፣ በገጠር ልማት፣ በትራንስፖርትና መገናኛ በመከተም...ወዘተ. የተነደፉትን ዕቅዶች ተግባራዊ በማድረግ የተገኙትን ውጤቶች ለመገምገምና ለመከታተል ይጠቅማል።

ሐ. <u>ከቆጠራው ውጤት የሚገኘው መረጃ ለአስተዳደር ሥራ ይጠቅማል</u>

ከቆጠራው ውጤት የሚገኘው መረጃ ለአስተዳደር የሚሰጠው ዐብይ ጥቅም ለሕዝባዊ ምርጫ የሚወሰኑትን የአስተዳደር ክልሎች ለመለየትና (Demarcation of constituencies) የመራጩንና የተመራጩን ሕዝብ ብዛት በማወቅ በአንድ ምርጫ ክልል ስንት ተወካዮች

እንደሚመረጡ ለመወሰን ይረዳል። በመሆኑም የሕዝቡን ጂኦግራፊያዊ ሥርጭት ማወቅ ሕዝባዊ ምርጫዎችን ለማስፈጸም በጣም አስፈላጊ ነው።

መ. <u>ከቆጠራው የሚገኘው መረጃ ለግብርና ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ የሠራተኛን አቅርቦትና ፍላጎት ለመለየት ይጠቅማል</u>

ከቆጠራው ውጤት የሚገኘው መረጃ በግብርና በንግድ እንደዚሁም በኢንዱስትሪ ለተሰማሩ ግለሰቦች ድርጅቶችና ለሠራተኛው ክፍል ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። መጠናቸውና ዓይነታቸው የተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ፍላጎትን ለማወቅና አገልግሎትን ለማሟላት የሕዝቡን ብዛት፣ ዕድሜ፣ ጾታና ስርጭት ማወቅ ያስፈልጋል። እነዚህ መረጃዎች ለሕዝቡ በሚቀርቡት የምግብ መጠንና ዓይነት፣ የልብስና የመጫሚያዎች ዓይነት፣ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ዓይነት፣ በሚሰጡት የትምህርት፣ የጤና፣ የመዝናኛ አገልግሎቶች ...ወዘተ. ላይ ከፍተኛ ወሳኝነት አላቸው። እነዚህን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ለማቅረብ የሚቋቋሙ ድርጅቶች የት መቋቋም እንዳለባቸው ምርቱን ለማምረትና አገልግሎቱን ለመስጠት የሚፈለገው ሠራተኛ በሚፈለገው መጠንና ችሎታ መኖር ወሳኝነት አለው።

ሠ. <u>ከቆጠራው የሚገኘው መረጃ ሕዝቡን በተመለከተ ለሚደረገው ጥናትና ምርምር ይጠቅማል</u>

ከቆጠራው የሚገኘው መረጃ የሕዝቡን ጥንቅር ማለትም በዕድሜ፣ በፆታ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በሥራ ዓይነት፣ በብሄረሰብ፣ በቋንቋ፣ ... ወዘተ. ስርጭት፣ የሕዝቡን ያለፈውን፣ የአሁኑንና የወደፊቱን የየዓመቱን ዕድገት መጠን፣ ሕዝብንና ልማትን፣ ... ወዘተ. በተመለከተ ሳይንሳዊ የሆነ ጥናት፣ ምርምር፣ ትንተናና ግምገማ ለማካሄድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። በተጨማሪም መረጃው የመለዋወጥ ባህርይ ያለውን የሕዝቡን የከተማና የገጠር ሥርጭት፣ የመከተም ሁኔታ፣ የሕዝቡን ጂኦግራፊያዊ ሥርጭት በሥራ ዓይነት፣ የትምህርት ተሳትፎ የትምህርት ደረጃ፣ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ መጠን፣ በጾታና በዕድሜ ሁኔታ፣ በሞት፣ በልደት፣ በፍልሰት መጠን፣ ...ወዘተ. በተመለከተ አንጻራዊ ጥናት ምርምርና ግምገማ ለማካሄድ ይጠቅማል።

ረ. <u>ወደፊት ለሚካሄዱ ጥናቶች መሠረት በመሆን ያገለግላል፣</u>

በየጊዜው የሚከሰቱትን ለውጦች በመገምገም ረገድ የቆጠራው ውጤት መሠረት በመሆን እንደሚያገለግል ሁሉ እንደዚሁም የተለያዩ ጥናቶችን ለማካሄድ ለሚደረገው ዝግጅትና የአሠራር ዘዴ ወይም ሜቶዶሎጂ ቅየሳ መሠረት በመሆን ይጠቅማል።

ሰ. <u>ቤቶችን በተለይም መኖሪያ ቤቶችን በሚመለከት ፖሊሲንና ፕሮግራሞችን ለመቀየስ አመች ሁኔታዎች ይፈጠራል፣</u>

መኖሪያ ቤቶችን በሚመለከት ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት በግንባር ቀደም የቤቶችን ሁኔታ የሚገልጹ እስታቲስቲካዊ መረጃዎች ያስፈልጋሉ። በተጨማሪ ከነዚህ መረጃዎች በመነሳት የተደረሰባቸውን ለውጦች ለመገምገም፣ ለወደፊት ሊኖር ስለሚችለው የቤት ፍላጎትና አቅርቦት ለመገመት ...ወዘተ. ይቻላል። ለነዚህ ሁሉ የቆጠራው ውጤት አስፈላጊ ይሆናል።

ሸ. <u>በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሕዝብና ቤቶችን በሚመለከት ለሚነሱት መሠረታዊ የመረጃዎች ጥያቄ የተሟላና አጥጋቢ መልስ ለመስጠት ያስችላል።</u>

አገራችን የተለያዩ ድርጅቶች ማለትም የተባበሩት መንግሥታት፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት፣ የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት፣ የዓለም ባንክ፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ እና የመሳሰሉት አህጉርና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች አባል እንደመሆና መጠን ከነዚህ ድርጅቶች በተለያየ ጊዜ ለሚቀርቡ ሕዝብና ቤት ነክ የመረጃ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት ያስችላል።

### 4.4 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሲካሄድ መሟላት ያለባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች

ሀ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማካሄድ የመንግሥት ኃላፊነት ነው፣

የቆጠራው ሥራ በጣም አስፈላጊ፣ ከፍተኛ ሥራና ወጪ እንደዚሁም የድርጅቶችና የግለሰቦችን ትብብር የሚጠይቅ በመሆኑ የሚከናወነው በመንግሥት ነው። ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የቆጠራው ሥራ በአዋጅ መደገፍ ስለአለበት የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈጸሚያ አዋጅ ማውጣት ያስፈልጋል።

ለ. የሕዝብና የቤት ቆጠራ ወሰኑ በታወቀ አስተዳደር ክልል ያለውን አካባቢ በሙሉ መሸፈን አለበት፣

ቆጠራው አንድ ወሰኑ በታወቀ የአስተዳደር ክልል ውስጥ ያለውን አካባቢ ሳይደጋገም ወይም ሳይዘለል ሙሉ በሙሉ መሸፈን አለበት። ወሰኑ የታወቀ የአስተዳደር ክልል ማለትም ወረዳ፣ ከተማ፣ ዞን፣ ብሄራዊ ክልል ወይም ሀገርን ሙሉ በሙሉ የሚያጠቃልል ማለት ነው።

ሐ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሁሉን አቀፍ መሆን አለበት:-

ቆጠራው ወሰኑ በታወቀ የአስተዳደር ክልል ነዋሪ የሆነውን ሕዝብና በክልሉ የሚገኘውን ቤት ሁሉ ሳይደገምና ሳይዘለል የሚያጠቃልል መመሆን አለበት።

መ. የሕዝብና የቤት ቆጠራ የነፍስ ወከፍ ቆጠራ መሆን አለበት:-

በቆጠራው የሚሰበሰበው መረጃ እያንዳንዱን ነዋሪ በነፍስ ወከፍ በየቤቱ ሄዶ በመጠየቅ የሚገኝ መልስመሆን አለበት። ይኸም ማለት የቀበሌውን ባለሥልጣን ወይም የመንደር ኃላፊውን ብቻ በመጠየቅ ስለቀበሌው ወይም ስለመንደሩ ነዋሪዎች የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃዎች መሰብሰብ አይኖርበትም ማለት ነው።

ሠ. የሕዝብና የቤት ቆጠራ በአንድ በተወሰነ ጊዜ መከናወን አለበት:-

ቆጠራው አንድ የተወሰነ ቀንና ሰዓትን በማስመልከት በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ መጠናቀቅ አለበት። ይኸውም ቆጠራው በአንድ በተወሰነ ቀን በእኩለ ሌሊት በቤተሰቡ የተገኙትን አባላት ወይም በዚያ ሰዓት የቤተሰቡ መደበኛ አባላት የነበሩትን ብቻ ያጠቃልላል። በመሆኑም

- ከዚያች ሰዓት በኋላ የሚወለደው ሕፃን በቆጠራው አይጠቃለልም፣
- ከዚያች ሰዓት በፊት የሞተም ሰው በቆጠራው አይጠቃለልም፣

ረ. የሕዝብና የቤት ቆጠራ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ይደገማል:-

የሕዝብና ቤት ቆጠራ በአብዛኛው አገሮች በየአሥር ዓመት ይካሄዳል። በጥቂት አገሮች ደግሞ በየአምስት ዓመቱ ይካሄዳል። ቆጠራው በተወሰነ ወቅት እንዲደገም ከሚያስገድዱ ምክንያቶች አንዱ በተከታታይ በተካሄዱ ቆጠራዎች የተገኙትን መረጃዎች ለማወዳደርና በሕዝቡ ብዛት ወይም በሕዝቡ ባሕርያት (የትምህርት ደረጃ፣ በልደት፣ በሞት፣...ወዘተ.) የሚከሰተውን ለውጥ ለመገምገም እንዲያስችል ነው።

## 5. የሕዝብና ቤት ቆጠራ በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ብሄራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሄደው በ1976 ነው። ከዚያ በፊት በተወሰኑ አካባቢዎች በአዲስ አበባ በ1953 እና በ1961 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሄደ ሲሆን ተመሳሳይ ቆጠራዎችም በሌሎች ጥቂት ትላልቅ ከተማዎች ተካሄደዋል።

በ1976 በብሄራዊ ደረጃ የተካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የአገሪቱን ሕዝብና ቤት አስመልክቶ በተለይም ስለ ሕዝቡ ብዛትና ሥርጭት፣ ስለ ሕዝቡ የተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባሕርያት እንዲሁም ስለ ቤቶች ሁኔታ በሚመለከት በየወቅቱ ለተነሱ የስታቲስቲካዊ መረጃዎች ጥያቄ ምላሽ በመስጠት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ቆጠራውን አካሄዶ ዳር ለማድረስ የተለያዩ አበይት ተግባራት ተከናውነዋል። ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የካርታ ሥራ ማከናወን የሕዝብና ቤት ቆጠራ መጠይቅ፣ የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች መመሪያዎች፣ የቆጠራ ቅጽ፣...ወዘተ. ማዘጋጀት፣ ቆጠራውን ማካሄድ ማለትም ተፈላጊዎችን መረጃዎች መሰብሰብ እና የተሰበሰቡ መረጃዎችን አቀናብሮና ገምግሞ በመተንተንና በሪፖርት መልክ በማዘጋጀት ዉጤቱን ለመረጃ ተጠቃሚዎች ማቅረብ ነበሩ።

በቅድሚያ ለቆጠራው የመስክ ሥራ ክንውን አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ሲባል አገሪቷን በቆጠራና በመቆጣጠሪያ ቦታዎች በመሸንሸን የሕዝብና ቤት ቆጠራ የካርታ ሥራ ተከናውኖአል። ለዚህም የመስክ ሥራ ክንውን ከ600 ሠራተኞች በላይ እንዲሳተፉ ሲደረግ ወደ 7.5 ሚሊዮን ብር የሚደርስ ወጪ ተደርጓል። የካርታውን የመስክ ሥራ ለማጠናቀቅ ወደ 30 ወራት ፈጅቷል።

ቆጠራው በግንቦት ወር 1976 የተካሄደ ሲሆን ከአገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ ወደ ሰማንያ አንድ በመቶ የሚሆነው በቆጠራው ሊሸፈን ተችሏል። በተዘጋጀው የቆጠራ ካርታ በመመስረት በቆጠራው ለተሸፈኑት ስለ እያንዳንዱ ቤተሰብና ቤት ተፈላጊዎቹ መረጃዎችን ከቤት ቤት በመሄድ ተሰብስበዋል። መረጃዎቹም በኮምፒዩተር ተቀነባብረው አስፈላጊው ግምገማና ትንተና ተካሄዶ የቆጠራውን ውጤት የሚያሳዩ የትንተና ሪፖርቶች ለየክፍለ ሃገሩና በብሄራዊ ደረጃም ተዘጋጅቶ የታተመ ሲሆን ሪፖርቶቹም ለተጠቃሚዎቹ ተሰራጭተዋል። ከላይ እንደተጠቀሰው ቆጠራው አገሪቱን በሙሉ ያላጠቃለለ በመሆኑ በቆጠራው ያልተሸፈኑ አካባቢዎች አሉ ማለት ነው። እነዚህም በየክፍለ ሃገሩ የሚገኙ ጠቅላላ የዘላን አካባቢዎች፣ በትግራይና በኤርትራ ክፍለ ሃገራት የገጠሩ አካባቢዎች በሙሉ፣ እንዲሁም በከፊል በጎንደር፣ በወሎና በሐረርጌ ክፍለ ሃገራት የገጠር አካባቢዎችን ያጠቃልላል።

ተፈላጊዎቹን መረጃዎች ለመሰብሰብና አቀናብሮም ለመረጃ ተጠቃሚዎች ለማቅረብ ከፍተኛ የሰው ኃይል፣ የገንዘብና የሎጅስቲክስ ድጋፍ ጠይቋል። የቆጠራው የመስክ ሥራ ክንውን ተግባር በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የተጠናቀቀ ሲሆን 43,372 መረጃ ሰብሳቢዎች፣ 8,007 ተቆጣጣሪዎች 3,437 የሚሆኑ የበላይ አስተባባሪዎች ተሰማርተዋል። ለቆጠራው ወደ 24.3 ሚሊዮን ብር የሚደርስ ወጪ የተደረገ ሲሆን ለካርታ ሥራ ከወጣው ወጪ ጋር ሲደመር በጠቅላላው ወደ 31.8 ሚሊዮን ብር በካፒታል በጀት ወጪ ተደርጓል። እንዲሁም ቆጠራውን ለማስፈጸም በመደበኛ በጀትም ወደ 7 ሚሊዮን ብር እንደወጣ ይገመታል። በመሆኑም በ1976 ለተካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የካፒታል በጀትና የመደበኛ በጀት ሲደመር በጠቅላላው ወደ 39 ሚሊዮን ብር ወጪ ሆኖአል።

የሕዝብና የቤት ቆጠራ ሥራ የአገሪቷ አንደኛው ብሄራዊና ከፍተኛ የስታቲስቲክስ ፕሮግራም እንደመሆኑ መጠን በአንድ ድርጅት ብቻ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል በቅድሚያ ግንዛቤ አግኝቶ ለዚሁ ሲባል የተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶችና ሕዝባዊ ድርጅቶችን በተቀናጀ መልክ ለማሳተፍ በሚያስችል አኳኋን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ተቋቁሞ ቆጠራው ተግባራዊ ለመሆን በቅቷል። በዚህ ውስጥ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ቆጠራውን በማቀድና በማደራጀት ተግባራዊ እንዲሆን በአስፈጻሚነት ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል። ኮሚሽኑ የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር ለመወጣት አመቺ በሚሆንበት መንገድ ከብሄራዊ ደረጃ አንስቶ እስከ ወረዳ ድረስ በኮሚቴዎችና በጽ/ቤቶች ተዋቅሮ ነበር።

በኮሚሽኑ የተዋቀሩት ኮሚቴዎችና ጽ/ቤቶች በየደረጃው ቆጠራው የሚጠይቀውን ሁሉ በማሟላት፣ አመራር በመስጠት፣ እንደአስፈላጊነቱ እርምጃ በመውሰድ፣ ለቆጠራው አፈጻጸም የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግና ቆጠራው በታቀደው ጊዜ መመሪያን ተከትሎ መፈጸሙን በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። የቆጠራውን ሕጋዊነት ለማረጋገጥና የኮሚሽኑን መቋቋም ዕውን ለማድረግ የሕዝብና ቤት ቆጠራ አዋጅ ቁጥር 252/ 1976 ታውጆ ነበር።

በ1976 የተካሄደው የሕዝብና የቤት ቆጠራ አደረጃጀቱና አፈጻጸሙ ከአስገኘው ውጤት ጋር ተዳምሮ በአፍሪቃ አህጉር ተመሳሳይ ቆጠራ ከአካሄዱ አገሮች ጋር ሲነጻጸርም ከፍተኛውን ቦታ እንደያዘ ይነገርለታል።

## 6. የ1987 አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ

### 6.1 የቆጠራው አስፈላጊነት

ከ1976 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተገኙትን መረጃዎች ወቅታዊ ለማድረግ፣ የተከሰቱትን ለውጦች ለመገምገም፣ አዳዲስ መረጃዎችንም በብቃትና በጥራት ለማስገኘት፣ የወደፊት የሥነ ህዝብ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ባህርያትን አስተማማኝና ወቅታዊ ከሆኑት መረጃዎች ላይ በመነሳት ለመተንበይ እንዲቻል፣ በተጨማሪም በ1976 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ያልተሸፈኑትን የሀገሪቷን ክፍሎችና ሕዝቦች ሙሉ በሙሉ ለመሸፈንና የሕዝብና ቤት ቆጠራ በየአሥር ዓመቱ መደገም ስላለበት ሁለተኛውን አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በ1987 ማካሄድ አስፈላጊ ነው።

### 6.2 በቆጠራዉ የሚሸፍነው አካባቢ

አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በመሠረቱ ቆጠራው በሚካሄድበት አገር ያለውን ሕዝብና ቤት ሙሉ በሙሉ መሸፈን አለበት። በመሆኑም ለሁለተኛ ጊዜ በሚካሄደዉ አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በኢትዮጵያ ክልል ዉስጥ የሚገኙትን የዘላን ሕዝቦችን ጭምር ለመሸፈን ታቅዷል።

### 6.3 ለቆጠራዉ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል

የሁለተኛዉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ከመጀመሪያው (ከ1976 ቆጠራ) ጋር ሲነጻጸር በሕዝብ ብዛትና በሚሸፍነዉ አካባቢ የላቀና ሠፊ በመሆኑ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ቁጥር ከፍተኛ ነው። የቆጠራዉ ቅድመ ዝግጅት አካል የሆነዉን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ካርታ ሥራ መስሪያ ቤቱ ለ17 ወራት ባካሄደዉና ቁተዘጋጁት የቆጠራና የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎች ብዛት መሠረት 84,900 የሚሆኑ (68,250 ቆጣሪዎች 13,650 ተቆጣጣሪዎች እንዲሁም 3,000 የሚሆኑ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የቆጠራ ጽ/ቤት ሠራተኞች) በቆጠራው ሥራ ይሳተፋሉ ተብሎ ይገመታል።

### 6.4 የሠራተኞች ምልመላ፣ ሥልጠናና ሥምሪት

ከላይ የተጠቀሱትን በቆጠራው የሚሠማሩ ሠራተኞች መመልመልና ቆጠራውን ለማካሄድ የሚያስችላቸውን ሥልጠና መስጠት ያስፈልጋል። በመሆኑም በቆጠራዉ ሥራ ለሚሠማራዉ የሰዉ ኃይል በሦስት ደረጃ ሥልጠና ለመስጠት ዕቅድ ወጥቷል። በዕቅዱም መሠረት፣

ሀ. በመጀመሪያ ዙር ሥልጠና ማለትም በአሠልጣኞች ሥልጠና የሚሣተፉ ወደ 200 የሚደርሱ ፕሮፌሽናልና መለስተኛ ፕሮፌሽናል የማ/ስ/ባ ባልደረቦች በዋናዉ መ/ቤት የ10 ቀናት ሥልጠና ከሐምሌ 13/1986 ጀምሮ ተሠጥቷል።

ለ. በሁለተኛ ዙር ወደ 3,600 ለሚደርሱ አሰልጣኞች በክልልና በዞን ደረጃ ሥልጠና እንዲሰጥ ታቅዶ ወደ 1,200 ለሚደርሱ በባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለሚገኙ የመስክ ሠራተኞች ከነሐሴ 2/1986 ጀምሮ የአሰልጣኞች ሥልጠና የተሠጠ ሲሆን በተመሣሣይ ደረጃ ለተቀሩት 2,400 ለሚደርሱ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራን ደግሞ ከመስከረም 2/1987 ጀምሮ በየክልሉና በየዞኑ የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል።

ሐ. በሦስተኛ ዙር በዋናዉ ቆጠራ ሥራ ላይ የሚሠማሩ 12ኛን ክፍል ያጠናቀቁ ወደ 68,250 የሚደርሱ ቆጣሪዎችን መመልመልና ማሠልጠን፣ እንዲሁም እነኚህን ቆጣሪዎች የሚቆጣጠሩ ወደ 13,650 የሚደርሱ መምህራንና ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች የመመልመል የማሠልጠንና ለቆጠራዉ ሥራ የማሰማራቱ ሂደት ይቀጥላል።

በመጀመሪያዉና በሁለተኛዉ ዙር በአሠልጣኝነት የሠለጠኑት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ፕሮፌሽናልና መለስተኛ ፕሮፌሽናል እንዲሁም የመስክ ሠራተኞች በዋናዉ ቆጠራ ለሚሠማሩ ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች አሠልጣኝ ከመሆናቸዉም በላይ በክልል በዞንና በወረዳ የቆጠራ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በመሆን የቆጠራዉን ሥራ እንዲያስተባብሩ ተመድበዋል።

## 6.5 ቆጠራው የሚወስደዉ ጊዜ

ሁለተኛዉ አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ በመላው አገሪቱ ከጥቅምት 1ቀን 1987 ጀምሮ እስከ አስር ቀናት ባለዉ ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ይገመታል።

## 6.6 በቆጠራው የሚሰበሰቡት መረጃዎች ዓይነት ትርጉምና ጽንሰ ሃሣብ፣

ሊካሄድ በታቀደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በገጠርና በከተማ በአብዛኛው ተመሳሳይ መረጃዎች የሚሰበሰቡ ቢሆንም የቤት መረጃን አስመልክቶ በገጠርና በከተማ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ለማንፀባረቅ ሲባል ከከተማ አኑዋኑዋር ጋር የሚጣጣሙ አንዳንድ ጥያቄዎች በከተማ ቆጠራ እንዲካተቱ ተደርገዋል። ከዚህ በተጨማሪም ከቤት ቤት በመሄድ ሰፋ ያለ መረጃ መሰብሰብ ብዙ ወጪና ጊዜን የሚጠይቅ በመሆኑ በሚደረገው ቆጠራ አጭር መጠይቅ በመጠቀም የተወሰኑ መረጃዎች ለሁሉም ቤተሰቦች ከቤት ቤት በመዘዋወር የሚሰበሰቡ ሲሆን ዝርዝር መረጃዎች ግን ረዥም መጠይቅ በመጠቀም በናሙና ለተመረጡ ቤተሰቦች ብቻ ከቤት ቤት በመዘዋወር ይሰበሰባሉ።

### 6.6.1 በከተማም፣ በገጠርም፣ አጭርና ረዥም መጠይቆች በመጠቀም የሚሰበሰቡ መረጃዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

#### ሀ. ለሁሉም ቤተሰቦች አጭር መጠይቅ በመጠቀም የሚሰበሰቡ መረጃዎች

1. የቤተሰብ መደበኛ አባላትና የእንግዶች ሙሉ ስም
2. የነዋሪ ሁኔታ
3. ጾታ
4. ዕድሜ
5. ሃይማኖት
6. የእፍ መፍቻ ቋንቋ
7. ተጨማሪ ቋንቋ የመናገር ችሎታ
8. ብሄረሰብ
9. የጋብቻ ሁኔታ

#### ለ. በናሙና ለተመረጡ ቤተሰቦች ረዥም መጠይቅ በመጠቀም የሚሰበሰቡ መረጃዎች

1. የቤተሰብ መደበኛ አባላትና የእንግዶች ሙሉ ስም
2. የነዋሪ ሁኔታ
3. ጾታ
4. ዕድሜ
5. ሃይማኖት
6. የእፍ መፍቻ ቋንቋ
7. ተጨማሪ ቋንቋ የመናገር ችሎታ
8. ብሄረሰብ
9. እዚህ ወረዳ ገጠር ውስጥ ያለማቋረጥ ስንት ዓመት ኖረዋል?
10. ቀደሞ ይኖሩበት የነበረው ሥፍራ ከተማ ወይም ገጠር ስለመሆኑ፣
11. የአካለ ጉዳተኝነት ሁኔታ
12. በትምህርት ቤት የመማር ሁኔታ

13. የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል (የማንበብና የመጻፍ ችሎታ)
14. በምርታማ ሥራ መሳተፍ
15. ሥራ ካልሠሩ ያልሠሩበት ምክንያት
16. የሥራ ዓይነት
17. የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት
18. የትዳር ሁኔታ
19. የጋብቻ ሁኔታ
20. በጠቅላላ በሕይወት የተወለዱ ልጆች ብዛት
21. ባለፉት 12 ወራት በሕይወት የተወለዱ ልጆች ብዛት

6.6.2 ስለመኖሪያ ቤቶች የሚሰበሰቡ መረጃዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፥

ሀ. <u>በገጠር</u>

1. የቤቱ ዓይነት
2. የቤቱ ግድግዳ በአብዛኛው ከምን እንደተሠራ
3. የቤቱ ጣሪያ በአብዛኛው ከምን እንደተሰራ
4. ቤቱ የመጠጥ ውሃ ከየት እንደሚያገኝ
5. የቤቱ ክፍሎች ብዛት
6. ቤቱ ያለው የመጸዳጃ አገልግሎት ዓይነት
7. ቤተሰቡ በሚያድርበት ቤት ከብቶች ያድሩ እንደሆነ
8. የቤቱ የማድቤት ሁኔታ
9. ቤቱ ለምግብ ማብሰያ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀመው የማገዶ ዓይነት
10. በቤቱ ሬዲዮ መኖር

ለ. <u>በከተማ</u>

1. የቤቱ አገልግሎት
2. በቤቱ ስንት መደበኛ ቤተሰቦች እንደሚኖሩ
3. በቤቱ ስንት መደበኛ የቤተሰብ (ቤተሰቦች) አባሎች እንደሚኖሩ
4. የቤቱ ዓይነት
5. ቤቱ የሚገኝበት የሕንፃ ዓይነት
6. የቤቱ ዕድሜ
7. የቤቱ ግድግዳ አብዛኛው ከምን እንደተሠራ
8. የቤቱ ጣሪያ አብዛኛው ከምን እንደተሠራ
9. የቤቱ ኮርኒስ አብዛኛው ከምን እንደተሠራ
10 የቤቱ ወለል አብዛኛው ከምን እንደተሠራ
11. የቤቱ ክፍሎች ብዛት
12. የቤቱ ይዞታ
13. ቤቱ የኪራይ ከሆነ በወር የሚከፈለው የኪራይ መጠን
14. ቤቱ የመጠጥ ውሃ ከየት እንደሚያገኝ
15. ቤቱ ያለው የማድቤት ዓይነት
16. ቤቱ ለምግብ ማብሰያ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀመው የማገዶ ዓይነት
17. ቤቱ ያለው የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ዓይነት

18. ቤቱ ያለው የመፀዳጃ አገልግሎት ዓይነት
19. ቤቱ ያለው የመብራት አገልግሎት ዓይነት
20. በቤቱ ሬዲዮ መኖር
21. በቤቱ ቴሌፎን መኖር
22. በቤቱ ቴሌቪዥን መኖር

6.6.3 ጽንሰ ሃሳቦችና ትርጓሜዎች፣ ለእያንዳንዱ ግለሰብና ድርጅት ቆጠራ ከመካሄዱ በፊት ስለ ተዘረዘሩት የመረጃዎች ዓይነትና ምንነት ለማሳወቅ ሲባል የመረጃዎች ትርጓሜና ጽንሰ ሃሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል። የዚህ ተግባር ዋና ዓላማ ግለሰቦችና ድርጅቶች የመረጃዎችን ዓይነትና ትርጉም ቆጠራው ከመካሄዱ በፊት አስቀድሞ ለማወቅ ስለሚያስችላቸው በቆጠራው ጊዜ ለሚጠየቁት ሁሉ ትክክለኛ መልስ ለመስጠት እንዲችሉ ነው።

ሀ. ስለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚሰበሰቡ መረጃዎችን በተመለከተ:-

1. ቤተሰብ፣ ቤተሰብ ማለት:-

ሀ. በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ አብረው የሚኖሩና፣

ለ. ምግባቸውን በአንድ ማዕድ ቤት አብስለው ከአንድ ማዕድ የሚመገቡ ግለሰቦችን ያጠቃልላል። ግለሰቦች የአንድ ቤተሰብ አባላት ናቸው ሊባል የሚቻለው እነዚህ ሁለት ነጥቦች ሲሟሉ ብቻ ነው። አንደኛው ተሟልቶ ሌላው ካልተሟላ የአንድ ቤተሰብ አባላት ናቸው ሊባሉ አይችሉም። የአንድ የቤተሰብ አባላት በሥጋ ወይም በጋብቻ ሊዛመዱ ይችላሉ። ለምሳሌ የአንድ ቤተሰብ አባላት ባል፣ ሚስት፣ ልጆች፣ የባል እናት፣ የሚስት ወንድም፣ የተቀጠረ እረኛና የተቀጠረች የቤት ሠራተኛ ... ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ።

አዲስ ትዳር የመሠረቱ ባልና ሚስት ደግሞ ብቻቸውን የሚኖሩና ከአንድ ማዕድ የሚመገቡ ከሆነ እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ። ብቻቸውን በአንድ ቤት የሚኖሩ ባልቴት ወይም አዛውንት ወይም ወንደ ላጤ ...ወዘተ.ምግብ ለብቻቸው እየተዘጋጀላቸው የሚመገቡና በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ እያንዳንዳቸው እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ። ምንም የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና የሌላቸው ሰዎችም በአንድ መኖሪያ ቤት የሚኖሩና ምግባቸው በአንድ ማዕድ ቤት እየተዘጋጀ ከአንድ ማዕድ የሚመገቡ ከሆነ እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ። ነገር ግን ምግባቸውን ለየግላቸው በማዘጋጀት ለየብቻ የሚመገቡ በአንድ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በአንድ ቤተሰብ ሊጠቃለሉ አይችሉም። ምክንያቱም ቤተሰብ ከሚያሰኙት ሁለት ነጥቦች አንደኛው አልተሟላምና ነው።

አንድ ወንድ ብዙ ሚስቶች ያሉት ሆኖ ሚስቶቹ በሙሉ ከነልጆቻቸው ከሰውየው ጋር በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የሚኖሩና ከአንድ ማዕድ በአንድነት የሚመገቡ ከሆነ ሁሉም እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ። ነገር ግን ሚስቶች እያንዳንዳቸው ከልጆቻቸውና ሌሎች ጥገኞቻቸው ጋር በተለየ ቤት ምግባቸውን ለየብቻ እያዘጋጁ የሚመገቡ ከሆነ እያንዳንዳቸው ከነልጆቻቸውና ከሌሎች ጥገኞቻቸው ጋር እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ። ስለሆነም ባልየው ካሉት ሚስቶች መካከል መጀመሪያ ካገባትና በሕይወት ከምትገኘው ሚስት ቤተሰብ ጋር እንደ አባል ሲቆጠር የቀሩት እያንዳንዳቸው ከነልጆቻቸውና ሌሎች ጥገኞች ጋር ራሳቸውን የቻሉ የተለያዩ ቤተሰቦች ይሆናሉ።

2. <u>መደበኛ የቤተሰብ አባል፥</u>

አንድ ግለሰብ የማንኛውም ቤተሰብ መደበኛ አባል ነው የሚባለው ቢያንስ ቢያንስ ያለማቋረጥ ለስድስት ወራት የዚያ ቤተሰብ አባል ሆኖ የተቀመጠ እንደሆነ ነው። ይህም ማለት ከቤተሰቡ ጋር በአንድ ቤት ወይም እንደ አንድ መኖሪያ ሊቆጠሩ በሚችሉ የተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ ከጋራ ማዕድ እየተመገቡ ያለማቋረጥ ቢያንስ ቢያንስ ለስድስት ወራት አብሮ የኖረ እንደሆነ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ግለሰቡ በእንግድነት ለአጭር ጊዜ (ማለት ጥቂት ቀናት) አልፎ አልፎ ወደ ሌላ ቦታ ወይም ቤት ቢሄድ አሁንም ግለሰቡ የቤተሰቡ መደበኛ አባል እንደሆነ ይቆጠራል። ከቤተሰቡ ጋር ለዘለቄታዉ ለመኖር የመጡ ሁሉ ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸዉም እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል ይቆጠራሉ። በተጨማሪም ሌላ መኖሪያ ቤት የሌለው መሆኑ ወይም የሌላ ቤተሰብ አባል ያለመሆኑ የታወቀ ከአንድ ቤተሰብ ጋር እንደ አባል ሆኖ የሚኖር ግለሰብ ስድስት ወር ባይሞላው በቆጠራው ጊዜ ከሚኖርበት ቤተሰብ ጋር እንደ መደበኛ አባል ሆኖ ይቆጠራል። ለምሳሌ ለትዳር ወደ ባልዋ ቤተሰብ የሄደች ሴት ስድስት ወር ባይሞላትም የባልዋ መደበኛ ቤተሰብ አባል ሆና ትቆጠራለች። በቋሚ እረኛነት፥ ዘበኝነት፥ የቤት ሠራተኛነት፥...ወዘተ. ተቀጥሮ ከተቀጠረበት ቤተሰብ ጋር እንደ አባል የሚኖር ሰዉ ስድስት ወር ባይሞላው የተቀጠረበት ቤተሰብ መደበኛ አባል ሆኖ ይቆጠራል። እንደዚሁም በቅርብ የቤተሰቡ አባል ከሆነች ሴት ከአንድ ወይም ሁለት ወር በፊት የተወለደ ሕፃን የቤተሰቡ መደበኛ አባል ነው። በተጨማሪም ያረጁ ሽማግሌዎች፥ አሮጊቶች ከቤተሰቡ ጋር አብረው ይኖሩ ከሆነ የቤተሰቡ መደበኛ አባል ናቸው። ነገር ግን ከቤተሰቡ ተለይተዉ ከሄዱ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸዉ ወይም ከስድስት ወር በላይ ለመቆየት አቅደዉ የሄዱ ከቤተሰቡ ከወጡ ስድስት ወር ባይሞላቸዉም እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል አይቆጠሩም።

3. <u>የቤተሰብ ኃላፊ</u>

ማንኛውም ቤተሰብ የቤተሰብ ኃላፊ አለው። የቤተሰቡ ኃላፊ የሚባለው በሌሎች የቤተሰብ አባላት እንደ ኃላፊ የሚቆጠር ወንድ ወይም ሴት አባል ነው። አብዛኛውን ጊዜ ወንድ የቤተሰብ ኃላፊ እንደሚሆን የተለመደ ቢሆንም አልፎ አልፎ ሴት የቤተሰብ ኃላፊዎች እንደሚኖሩ መገንዘብ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ወጣት ልጆቻቸውን ብቻ ይዘው በአንድ መኖሪያ ቤት የሚኖሩ ሴት የቤተሰባቸው ኃላፊ ናቸው። ከወጣት ልጆቻቸውና ሌሎች ጥገኞች ጋር በተለያዩ ቤተሰቦች ውስጥ የሚኖሩ አራት የአንድ ሰው ሚስቶች ቢኖሩ ከመጀመሪያይቱ ሚስት በስተቀር የቀሩት ሶስቱ የየራሳቸው ቤተሰብ ኃላፊ ናቸው።

4. <u>የነዋሪነት ሁኔታ፥</u>

የማንኛውም ቤተሰብ አባላት በቆጠራው ዕለት በመደበኛ አባልነት በመኖሪያ ቤታቸው በመገኘታቸው ወይም ባለመገኘታቸው ወይም በእንግድነት የሚኖሩ በመሆናቸው ምክንያት በሶስት ይከፈላሉ።

ሀ. <u>በዕለቱ በቤት የነበሩ ነዋሪ</u>

በቆጠራው ዕለት በእንግድነት ወደ ሌላ ቦታ ወይም ቤት ሳይሄዱ ከመኖሪያ ቤታቸው የተገኙ መደበኛ አባላት እያንዳንዳቸው በዕለቱ በቤት የነበሩ ነዋሪ ይባላሉ።

ለ. <u>በዕለቱ በቤት ያልነበሩ ነዋሪ</u>

በቆጠራው ዕለት ለአጭር ጊዜ በእንግድነት ወደ ሌላ ቦታ ወይም ቤት በመሄዳቸው ምክንያት መደበኛ አባል የሆኑበት ቤተሰብ በሚኖርበት መኖሪያ ቤት ያልተገኙ መደበኛ አባላት እያንዳንዳቸው በዕለቱ "በቤት ያልነበሩ ነዋሪ" ይባላሉ።

ሐ. <u>በዕለቱ ቤት የነበሩ እንግዳ</u>

በቆጠራው ዕለት ቆጠራው በሚካሄድበት ቤት ውስጥ በሚገኘው ቤተሰብ መደበኛ የቤተሰብ አባል ሳይሆኑ በእንግድነት የተገኙ ሰዎች በዚሁ ቤተሰብ ሥር በዕለቱ ቤት የነበሩ እንግዳ ተብለው ይቆጠራሉ።

በእንደዚህ ያለ ሁኔታ በቆጠራው ዕለት በእንግድነት የሚገኙ ሰዎች ሁሉ መደበኛ አባል ከሆኑበት ቤተሰብ ጋር በመኖሪያ ቤታቸው በዕለቱ በቤት ያልነበሩ ነዋሪ ሆነው ሲቆጠሩ በእንግድነት ከሚገኙበት ቤተሰብ ጋር ደግሞ እንደ እንግዳ ሆነው ይቆጠራሉ። ስለሆነም አንድ ቤተሰብ ከላይ የተገለጹትን ሶስቱን የነዋሪ ሁኔታዎች ወይም ሁለቱንም የነዋሪ ሁኔታዎች ወይም አንዱን ሁኔታ የሚያሟሉ ግለሰቦችን በቆጠራው ዕለት ሊይዝ ይችላል። ለምሳሌ በተጠቀሰው ቤተሰብ ውስጥ በቆጠራው ዕለት የቤተሰቡ መደበኛ አባላት በሙሉ ተገኝተው በተጨማሪም በእንግድነት ግለሰቦች ሊገኙ ይችላሉ። ወይም ደግሞ ከመደበኛ የቤተሰብ አባላት በቆጠራው ዕለት ከመኖሪያ ቤታቸው ሳይገኙ በሌላ ቤተሰብ መኖሪያ ቤት እንግዳ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ።

<u>እንግዳ፣</u>

እንግዳ ማለት የሕዝብና ቤት ቆጠራ በተካሄደበት ዕለት በተገኘበት ቤት ወይም ቤተሰብ መደበኛ ነዋሪና መደበኛ አባል ያልሆነ ግለሰብ ነው። በተጨማሪ የራሱ መኖሪያ ቤትና ቤተሰብ ያለው ግለሰብ በቆጠራው ዕለት የተገኘበት ቤት ውስጥ ወይም ቤተሰብ ጋር በተከታታይ ሲኖር ከስድስት ወራት ካልበለጠው ይህ ግለሰብ በተገኘበት ቤተሰብ እንግዳ ይባላል።

<u>የጋርዮሽ መኖሪያ፣</u>

ብዙ ሰዎች ከመደበኛ ቤተሰብ አኑዋኑዋር ውጪ በአንድ ቤት ወይም ቤቶች በአንድነት እየኖሩ በቤቱ ወይም በቤቶቹ ያሉትን መገልገያዎች ማለት ውኃን፣ መብራትንና ሌሎች አገልግሎቶችን በጋራ ወይም በሕብረት የሚጠቀሙበትና በአንድ መንግሥታዊ ወይም ሕዝባዊ ወይም የግለሰብ ድርጅት የሚኖሩበት ቤት ወይም ቤቶች የጋርዮሽ መኖሪያ ይባላል።

የጋርዮሽ መኖሪያ ሆቴሎች፣ ሆስፒታሎች፣ ወህኒ ቤት፣ የሕፃናት ማሳደጊያ፣ የአእምሮ በሽተኞች መታከሚያ፣ አዳሪ ትምህርት ቤቶች፣ የወታደር ካምፖች። ያረጁ ሰዎች መጦሪያ፣ የጸባይ ማረሚያዎች፣ አድባራትና ገዳማት፣ የሥራ ካምፖች፣ ...ወዘተ. ያጠቃልላል። እዚህ ላይ ሆቴሎችንና ሆስቴሎችን በሚመለከት መታወቅ ያለበት ነጥብ፣ አንድ ግለሰብ ሌላ ቦታ መኖሪያ ቤት ኖሮት በቆጠራው ዕለት ሆቴሉ ወይም ሆስቴሉ ውስጥ ቢገኝ፣ ወይም ሆቴሉ ወይም ሆስቴሉ ውስጥ ሲኖር ስድስት ወር ካልሞላው ይህ ግለሰብ የሚቆጠረው የሆቴሉ ወይም የሆስቴሉ እንግዳ እንጂ የሆቴሉ/የሆስቴሉ ነዋሪ ተብሎ አይደለም።

በጋርዮሽ መኖሪያ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ግለሰቦች ከጋርዮሽ መኖሪያ ግቢ ለብቻቸው ወይም ከቤተሰብ ጋር ሊኖሩ ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች አኑዋኑዋር እንደመደበኛ ቤተሰብ በመሆኑ የሚቆጠሩት እንደመደበኛ ቤተሰብ ነዋሪ ይሆናል።

7. <u>*መኖሪያ ቤት የሌላቸው ሰዎች፣*</u>

በእግር መንገድ፣ በመኪና መንገዶች ዳር፣ በተሽከርካሪዎች ማቆሚያ፣ በቤተክርስቲያንና በመስጊዶች ጥግ፣ በመቃብር ቤት እና በመሳሰሉት ቦታዎች ተኝተው የሚያድሩ ሰዎች መኖሪያ ቤት የሌላቸው ሰዎች ይባላሉ። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ተኝተው የሚያድሩበት ቦታ የተወሰነ ላይሆን ይችላል። የሚካሄደው የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ እንደዚህ ዓይነት ሰዎችን ያጠቃልላል።

8. <u>*ዕድሜ፣*</u>

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ ዕድሜው ስንት እንደሆነ ተጠይቆ ይመዘገባል። ስለዚህ ዕድሜ ምን ማለት እንደሆነና እንዴት በትክክል ሊታወቅ እንደሚችል እያንዳንዱ ግለሰብ ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። ዕድሜ ሲባል አንድ ሰው ከተወለደበት ዕለት ጀምሮ እስከሚቆጠርበት ዕለት ድረስ ያለውን ጊዜ በሙሉ ዓመት ማለት ነው። በዚህ ቆጠራ እስከ መስከረም 30/1987 ድረስ ያለዉ እድሜ በሙሉ ዓመት ይመዘገባል። ሙሉ ዓመት ማለት የአንድ ሰው ዕድሜ የተወሰነ ዓመታት ሆኖት በተጨማሪም ከአንድ ዓመት የሚያንሱ ወሮች ካሉበት ወሮቹን ትቶ ሙሉ ዓመታቱን ብቻ መውሰድ ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ ልጅ ዕድሜው 13ዓመት ከ11 ወር ከ3 ሳምንት ከሆነ የሚወሰደው የልጁ ዕድሜ 13 ዓመት ብቻ መሆኑን ነው። የሰውየው ዕድሜ በዓመት በወርና በሳምንት ከተሰጠ ዕድሜው በሙሉ ዓመት ብቻ ይመዘገባል። አንድ ሕፃን ልጅ ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ ዕድሜው 0 ሲሆን አንድ ዓመት ሞልቶት ከሁለት ዓመት በታች ከሆነ ደግሞ ዕድሜው 1 ዓመት ይሆናል። የአንድ ልጅ ዕድሜ 2 ዓመት አልፎት ከ3 ዓመት በታች ከሆነ ዕድሜው 2 ዓመት ይሆናል ... ወዘተ.።

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ዕድሜውን በትክክል ለማወቅ እንዲችል የተወለደበትን ጊዜ የአካባቢ ታሪካዊ ክንውኖች ከተፈጸሙባቸው ዕለታት ጋር ማገናዘብ ይኖርበታል። ከቤተሰቡ አባሎች ወይም ጎረቤት መካከል የአንዱን ዕድሜ በትክክል የሚያውቁ ከሆነ ከዚህ ሰው ዕድሜ ጋር በማገናዘብ ዕድሜአቸውን ማወቅ ይችላሉ። ለምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ እናቶች በየሁለት ወይም በየሶስት ዓመት ይወልዳሉ። የአንድ ልጅ ዕድሜ 7 ዓመት መሆኑ በትክክል ከታወቀ የእሱ ታላቅ ልጅ ዕድሜ 9 ሊሆን ይችላል በማለት መገመት ይቻላል። አንዳንድ ዕድሜአቸው የገፉ ሰዎች ለመከበር ሲሉ ዕድሜአቸውን ከፍ አድርገው ሊናገሩ ይችላሉ። ይኽ ትክክል አለመሆኑ መገለጽ አለበት። አንድ አባል ባገቡበት ጊዜ ዕድሜአቸው ስንት እንደነበር፣ ተጋብተው ስንት ዓመት እንደቆዩና እንደዚሁም ከልጆቻቸው ዕድሜ ጋር በማዛመድ ዕድሜአቸውን ለማወቅ ይችላሉ። ስለዚህ ዕድሜአቸውን በትክክል የማያውቁ ሰዎች ከላይ በተጠቀሱ ዘዴዎች በመጠቀም ትክክለኛ ዕድሜአቸውን ማወቅ ይኖርባቸዋል።

9. <u>*ኃይማኖት፣*</u>

ኃይማኖት ማለት አንድ ግለሰብ የሚከተለው እምነት ወይም የመንፈሳዊ ድርጅት አባልነት ነው። በቆጠራዉ ጊዜ እያንዳንዱ ግለሰብ የምን ኃይማኖት ተከታይ እንደሆነ ይጠየቃል። ማለትም የእስልምና የክርስትና /ኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክ፣ የፕሮቴስታንት/፣ የባህላዊ ዓምልኮት፣ ... ወዘተ።

10. <u>የአፍ መፍቻ ቋንቋ</u>

እያንዳንዱ ግለሰብ አፉን የፈታበት ቋንቋ ተጠይቆ ይመዘገባል። የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚባለው ግለሰቡ በሕፃንነቱ ወቅት ከወላጆቹ ወይም ከአሳዳጊዎቹ ጋር ይነጋገርበት የነበረው ቋንቋ ነው። ግለሰቡ አፉን የፈታበትን ቋንቋ በቆጠራው ወቅት ላይጠቀምበትም እንደሚችል ማስታወስ ይገባል።

11. <u>ተጨማሪ ቋንቋ የመናገር ችሎታ</u>

እያንዳንዱ ግለሰብ አፉን ከፈታበት ቋንቋ ሌላ ተጨማሪ ቋንቋ የሚያውቅ መሆኑ ተጠይቆ ይመዘገባል። ግለሰቡ ሌላ ቋንቋ ያውቃል የሚባለው በቋንቋው መልዕክቱን በትክክል ማስተላለፍና መቀበል የሚችል ከሆነ ብቻ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ምናልባት ግለሰቡ አፉን ከፈታበት ቋንቋ በተጨማሪ ሌሎች ከአንድ የበለጡ ቋንቋዎችን የሚያውቅ ከሆነ ከሁሉም ቋንቋዎች በይበልጥ የሚያውቀው ቋንቋ ተጨማሪ ቋንቋ ተብሎ ይወሰዳል።

12. <u>የጋብቻ ሁኔታ፣</u>

ዕድሜያቸው 10 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ወንድም ሴትም የቤተሰብ አባላት የጋብቻ ሁኔታ ይጠየቃል። የጋብቻ ሁኔታ በአራት ይከፈላል:-

ሀ. አግብተው የማያውቁ:- በሕይወታቸው ፈጽሞ ባል/ሚስት አግብተው የማያውቁ ማለት ነው።

ለ. በትዳር ላይ ያሉ:- መረጃው በሚሰበሰብበት ጊዜ ወይም በሕዝብ ቆጠራው ጊዜ በጋብቻ/በትዳር ላይ ያሉ ማለት ነው። ጋብቻቸው በሕግ ወይም በባሕል መሠረት ሳይፈርስ ነገር ግን ባለመግባባት የተነሳ ባልና ሚስቶች ተለያይተው የሚኖሩ ቢሆንም በትዳር ላይ እንዳሉ ይቆጠራል።

ሐ. ባለቤታቸው የሞቱባቸው:- የመጨረሻ ባላቸው/ሚስታቸው ሞተው ከዚያ ወዲህ ያላገቡት ማለት ነው። ከዚያ ወዲህ አግብተው በትዳር ላይ ካሉ በትዳር ላይ ያሉ ይባላሉ። ሁለት ወይም ሶስት ሚስቶች የነበሩዋቸው ሰው አንድ ሚስት ሞተውባቸው ከሆነ ሌላ ሚስት ስላላቸው እንደ ባለትዳር ይቆጠራሉ።

መ. የተፋቱ:- የመጨረሻ ጋብቻቸው (ትዳራቸው) ፈርሶ ሕጋዊ ወይም ባሕላዊ ፍቺ አድርገው ከዚያ ወዲህ ያላገቡ ማለት ነው። ብዙ ሚስቶች የነበሩአቸው ሰው ከአንድ ሚስት ጋር ቢፋቱ ሌላ ሚስት ስላላቸው ሰውየው በትዳር ላይ እንዳሉ ይቆጠራል።

13. <u>ብሄረሰብ፣</u>

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል (የተወለደ ሕፃንና በዕድሜ በጣም የገፉ ሽማግሌዎች ሳይቀር) ብሄረሰባቸው ምን እንደሆነ ተጠይቆ የብሄረሰቡ ስም ይመዘገባል። ብሄረሰብ የሚባሉት እንደ ሲዳማ፣ ወላይታ፣ ኩናማ፣ ጉራጌ፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግራይ፣ ሱማሌ፣ አገው፣ ኑዌር፣ አፋር፣ ...ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው እንጅ እንደ ቆቱ፣ ቦርጂ፣ ሜጫ፣ ... ወዘተ. ያሉ የኦሮሞ ክፍሎች ወይም እንደ መንዜ፣ ቡልጌ፣ ጎጃሜ፣ ... ወዘተ. ያሉት የአማራ ክፍሎች ...ወዘተ.

ብሄረሰቦች አይደሉም። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የተለያየ ብሄረሰብ ያላቸው ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ መታወቅ አለበት። ዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ ላልሆኑት ሁሉ በፓስፖርታቸው የተመለከተው ዜግነታቸው ይመዘገባል። ለምሳሌ አንድ አፍሪካዊ ቢኖር ዜግነቱን እንዲሁ አፍሪካዊ ተብሎ መነገር የለበትም። በትክክለኛ የማን አገር ዜጋ እንደሆነ መጠቀስ አለበት። ለምሳሌ ሱዳናዊ፣ ናይጀሪያዊ፣ ... ወዘተ. ተብሎ መመዝገብ አለበት።

14. <u>የፍልሰት ሁኔታ</u>

<u>በእዚህ ወረዳ ገጠር ውስጥ ያለማቋረጥ ለስንት ዓመት ኖረዋል</u>?

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ቆጠራው በሚካሄድበት ወረዳ ገጠር ክፍል ከመቼ ጀምረው በመኖር ላይ እንደሚገኙ ተጠይቀው የጊዜው ርዝማኔ ይመዘገባል። ግለሰቡ በወረዳው የገጠሩ ክፍል ውስጥ ተወልደው እስከ ቆጠራው ቀን ድረስ ከወረዳው ገጠር ውጭ ኑረው የማያውቁ ከሆነ ከልደት ጀምሮ መሆኑ ሲገለጽ ከተወለዱ ጀምሮ በወረዳው ገጠር ክፍል ውስጥ ሳልኖሩ ግለሰቦች በወረዳው ገጠር ክፍል መኖር ከጀመሩ ያለማቋረጥ ምን ያህል ዓመታት እንደሆናቸው ይጠየቃሉ።

አንዳንድ ግለሰቦች ከወረዳው ውጭ በሚገኝ ሆስፒታል ቢወለዱም የተወለዱበት ሥፍራ ተብሎ የሚቆጠረው የመኖሪያ ሥፍራቸው ነው እንጂ ሆስፒታሉ የሚገኝበት ወረዳ አይደለም። በተመሳሳይ መልክም እናትየው ዘመዶቿ በሚኖሩበት አካባቢ ልጅ ወልዳ፣ ታርሳ ብትመለስ ልጁ የተወለደበት ሥፍራ ተብሎ የሚቆጠረው የቤተሰቡ መደበኛ ሥፍራ እንጂ የእናትየው ዘመዶች የሚገኙበት ሥፍራ አይደለም። ከተወለዱ ጀምረው በወረዳው ገጠር ውስጥ ያልኖሩ የሚባሉት ግለሰቦች በሁለት መልክ ይከፈላሉ። እነርሱም:-

1. ከወረዳው የገጠር ክፍል ውጭ የተወለዱ እና
2. በወረዳው የገጠር ክፍል ውስጥ ተወልደው በመሀሉ በሌላ ወረዳ (ወይም በወረዳው ውስጥ በሚገኝ ከተማ) ሲኖሩ ቆይተው የተመለሱ ናቸው።

ከወረዳው የገጠር ክፍል ውጪ ለተወለዱ ግለሰቦች ያለማቋረጥ የኖሩበት ጊዜ የሚለው ወደ ወረዳው ገጠር ክፍል ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ስንት ዓመት እንደሆናቸው ሲሆን በወረዳው የገጠር ክፍል ውስጥ ተወልደው በመሀሉ በሌላ ወረዳ (በወረዳው ውስጥ በሚገኝ ከተማ) ሲኖሩ ቆይተው ለተመለሱ ግለሰቦች ደግሞ የሚመዘገበው ወደ ወረዳው ገጠር ክፍል ተመልሰው መጥተው መኖር ከጀመሩ ጊዜ ጀምሮ ያለማቋረጥ የኖሩበት ጊዜ ነው።

15. <u>የአካለ ጉዳተኝነት ሁኔታ</u>፣

ሲወለድ ወይም ከተወለደ በኋላ የሰውነት፣ የአእምሮ፣ ወይም የሌላ አበይት የሆኑ የአካል ክፍል መበላሸት የደረሰበት ግለሰብ አካለ ስንኩል ይባላል። ይኸ ግለሰብ የአካሉ ክፍል በመሰናከሉ፣ በመጎዳቱ ምክንያት ሌሎች ደህና የሆኑ ሰዎች ሊያከናውኑት የሚችሉትን ተግባራት (ትምህርት መከታተል፣ መዝናናትና ሌሎች የማኅበራዊ ነክ የሆኑ ተግባራት፣ የዕለት ጉርሱን ለማግኘት የሚያደርጋቸው ተግባራት፣ ...ወዘተ.) በሙሉ ወይም በከፊል ለማከናወን ባለመቻሉ የሶሺያልና የኢኮኖሚ ተግባራትን አሟልቶ በማከናወን ረገድ የተጓጎለ ነው።

16. <u>የትምህርት ሁኔታ፣</u>

በቆጠራው ወቅት ከሚሰበሰቡት የሕዝብ ማኅበራዊ ባሕሪያት አንዱ የሕዝብን የትምህርት ሁኔታ የሚመለከት ይሆናል። ይኸውም ዕድሜው አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ የቤተሰብ አባል ቆጠራው በሚካሄድበት ጊዜ በመማር ላይ መሆኑ፣ አሁን በመማር ላይ ካልሆነ ደግሞ ከዚህ በፊት ትምህርት ቤት ገብቶ ተምሮ የሚያውቅ ወይም የማያውቅ መሆኑንና አሁን በመማር ላይ ከሆነ የሚማርበትን የክፍል ደረጃ የሚያመለክቱ መረጃዎች ይሰበሰባሉ። አንድ ግለሰብ በመማር ላይ ነው የሚባለው በመደበኛ ትምህርት ቤት፣ በዩኒቨርስቲ፣ በኮሌጅ፣ በማሠልጠኛ ተቋም፣ በቄስ፣ በቁርዓን ወይም በሌሎች አነስተኛ የትምህርት ዝግጅት (ካሪኩለም) ባለው የትምህርት መስጫ ተቋም ውስጥ በመማር ላይ ሲሆን ነው። የቤተሰብ አባል ማንበብና መጻፍ የሚችል ከሆነ አሁን በመማር ላይ ቢሆንም ባይሆንም የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል ደረጃን በሚመለከት መረጃዎች ይሰበሰባሉ።

አንድ ግለሰብ የማንበብና የመጻፍ ችሎታ አለው የሚባለው በማንኛውም ቋንቋ አንብቦ መረዳትና እንዲሁም መጻፍ ሲችል ነው። የራሳቸውን ስም ወይም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ግለሰቦች የትምህርት ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም። እንዲሁም ኃይማኖት ነክ የሆኑና ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ አረፍተ ነገሮችን ብቻ ማነብነብ የሚችሉ ሁሉ የትምህርት ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም።

የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል የሚጠየቀው የማንበብና የመጻፍ ችሎታ አለን ያሉትን ሁሉ ሲሆን ይህም አሁን በመማር ላይ ያሉና ከዚህ በፊት የተማሩትንም ያጠቃልላል። የጨረሱት ክፍል ሲባል ግለሰቦች ባለው የትምህርት ሥርዓት ያጠናቀቁትን ከፍተኛ የትምህርት ክፍል የሚያመለክት ነው። ይኸም በክፍል ወይም በደረጃ ሊለካ ወይም ሊተረጎም የሚችል ሆኖ ማንኛውም በመደበኛ ትምህርት ወይም በዩኒቨርሲቲ የሚካሄድ ትምህርትና እንዲሁም ከዚህ ውጭ በማሠልጠኛ ተቋሞችና በመሳሰሉት የሚካሄደውን ትምህርት ያጠቃልላል።

<u>የሥራ ሁኔታ፣</u>

በሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ወቅት ከሚሰበሰቡት መረጃዎች መሐከል የኢኮኖሚ ሁኔታን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ይገኛሉ። ይኸ መረጃ የሚሰበሰበው ዕድሜያቸው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ የቤተሰብ መደበኛ አባላት ነው። ይኸ ጥያቄ በገጠር ዕድሜው አሥር ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የቤተሰብ አባል ቆጠራው ከመጀመሩ በፊት ባለፉት 12 ወራት ለምን ያህል ጊዜ <u>ምርታማ ሥራ</u> መሥራትና አለመሥራቱን፣ ከሠራ ለምን ያህል ጊዜ፣ የሥራው ዓይነት፣ የሚሠራበት ድርጅት፣ ካልሠራ ደግሞ ያልሠራበትን ምክንያት ሲጠየቅ በከተማም ተመሳሳይ ጥያቄዎች ዕድሜው አሥር ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆነ የቤተሰብ አባል ቆጠራው ከመጀመሩ በፊት ባለፉት ሰባት ቀናት ምርታማ ሥራ መሥራቱንና ስንት ቀን እንደሠራ ይጠየቃል።

<u>ምርታማ ሥራ ማለት</u> የሥራው ውጤት የሆነውን ሸቀጣ ሸቀጥ አገልግሎት በገንዘብም ሆነ በዕቃ በመለወጥ ገቢ ለማግኘት ለገበያ ለማቅረብ ሲቻል ነው። በራስ፣ በቤተሰብ ይዞታ፣ በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች በግለሰብ ድርጅት በቀን፣ በሳምንት፣ በወር ወይም በሠሩበት መጠን ክፍያ ወይም ገቢ ለማግኘት ሥራ ሲሠሩ ነው።

18. <u>ልደት፣</u>

በቆጠራው ከሚሰበሰቡት መረጃዎች መሀከል ልደትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ይገኛሉ። ልደትን በሚመለከት የሚጠየቁ የቤተሰብ አባላት ዕድሜያቸው አሥር ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሴቶች ሲሆን ጥያቄውም በጠቅላላው ሕይወት ኖሮአቸው የተወለዱ ልጆች ስንት እንደሆኑና ባለፉት 12 ወራት ሕይወት ኖሮአቸው የተወለዱ ልጆች ስንት እንደሆኑ ነው። እዚህ ላይ "ሕይወት ኖሮዋቸው የተወለዱ" ማለት አንድ ሕፃን እንደተወለደ ሕይወት ያለው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነው። በአጠቃላይ ሕይወት ኖሮአቸው የተወለዱ ልጆች ብዛት በውርጃና በሞት የተወለደውን አይጨምርም።

ለ. <u>ስለእያንዳንዱ ቤት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን በተመለከተ:-</u>

በብሄራዊ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የሚሰበሰቡት መረጃዎች የሕዝቡን ብዛትና ስርጭት፣ የሕዝቡን ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መሰል ባሕሪያትን ብቻ የሚመለከቱ ሳይሆን ስለ ቤቶች ብዛትና ስለሚሰጡት አገልግሎት እንዲሁም ስለመኖሪያ ቤቶች ሁኔታ የሚገልጹ መረጃዎችንም ለማስገኘት ጭምር ነው። ይህን መረጃ በትክክል ለመሰብሰብ እንዲቻል በቅድሚያ " ቤት፣ የቤት አገልግሎት፣ የመኖሪያ ቤት መገልገያዎችና ክፍል" የተባሉት ፅንሰ ሀሳቦች ምን ማለት እንደሆኑ ማወቅ ያስፈልጋል።

1. <u>ቤት</u>፣ ቤት ማለት በአሠራሩ ተለይቶ "ራሱን የቻለ" ሆኖ ለመኖሪያ ብቻ ወይም ለመኖሪያና ለድርጅት ወይም ለድርጅቱ ብቻ የሚያገለግል ነው።

   ሀ. <u>የቤቱ አሠራር የተለየ ነው</u> የሚባለው ዙሪያውን በግድግዳ፣ የተከለለ ሆኖ ጣራውም በክዳን የተሸፈነ በመሆኑ በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች በሚተኙበት ጊዜ፣ ምግባቸውን ሲያዘጋጁና ሲመገቡ ከሌሎች በዙሪያው ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ለመለየት የሚያስችል ሲሆን ነው። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ በሳጠራ፣ በፕላስቲክ፣ በካርቶን፣ ... ወዘተ. ግድግዳው የተሠራ ወይም የተከበበና ጣራው በፕላስቲክ ክዳን የተሸፈነ ሆኖ ቁመቱና የወለሉ ስፋት በጣም ያነሰ ለድርጅት ወይም ለመኖሪያ የሚያገለግል ቤት ሊያጋጥም ይችላል። ይኸ ሁኔታ ሲያጋጥም ምንም እንኳን የቤትን ትርጉም ባያሟላም ከአገልግሎቱ አንጻር ሲታይ ቤት ስለሆነ እንደቤት ይወሰዳል።

   ለ. <u>የቤቱ አሰራር ራሱን የቻለ ነው</u> የሚባለው ቤቱ ከመንገድ ወይም የጋራ በሆነ ደረጃ፣ መሬት... ወዘተ. የራሱ መግቢያና ወይም መውጪያ ያለው ሆኖ በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች ወደ ቤት ሲገቡ ወይም ከቤት ሲወጡ የሚተላለፉት በሌሎች ቤት ውስጥ በማለፍ ሳይሆን በቀጥታ በራሳቸው ቤት መውጫ ወይም መግቢያ ብቻ ሲሆን ነው።

2. <u>የቤቱ አገልግሎት</u> በቆጠራው ቀን ቤቱ የሚሰጠው አገልግሎት ይመዘገባል። የአገልግሎት አይነቶች ከዚህቀጥሎ ተዘርዝረዋል።

   ሀ. ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ
   ለ. ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት
   ሐ. ለሆቴል/ሆስቴል

መ. ሌላ ጋርዮሽ

ሠ. ለድርጅት ብቻ

ከዚህ ቀጥሎ ለእያንዳንዱ የቤት አገልግሎት ዓይነት ትርጉም ተሰጥቷል።

ሀ. ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ፣ በቆጠራው ቀን ቤቱ የሚሰጠው አገልግሎት ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያ ብቻ የዋለ ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ" ይባላል።

ለ. ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት፣ በቆጠራው ቀን ቤቱ የሚሰጠው አገልግሎት በከፊል ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያና በከፊል ደግሞ ለድርጅት አገልግሎት የዋለ እንደሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለመደበኛ ቤተሰብ መኖሪያና ለድርጅት" ይባላል። ድርጅት ማለት በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ያለው አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ የሰፕል ወይም የኤኮኖሚ ተቋም ነው። ይኸውም የማምረቻ፣ የአገልግሎትና የንግድ ተቋሞችን ያጠቃልላል። ለምሳሌ ጫማ፣ ዳቦ፣ ጨርቃ ጨርቅ ... ወዘተ. አምራቾች፣ የጫማ እድሳት፣ የትራንስፖርት፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የሕግ፣ የምግብና የመጠጥ አገልግሎትና ልዩ ልዩ ሽቀጣ ሸቀጥ ንግድ የሚያከሄዱትን ሁሉ ያጠቃልላል። ስለሆነም የቤቱ አገልግሎት ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት የሚባለው በአንድ ቤት ውስጥ የቤተሰብ አባላት እየኖሩበት እዚያው ውስጥ ከላይ ከተጠቀሱት የድርጅት ዓይነቶች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተግባራት ሲያከናውኑበት ነው።

ይኸውም ለምሳሌ:-

ቤቱ ለመኖሪያ ለመጠጥ መሸጫ (ጠላ፣ ጠጅ፣ ሌሎች መጠጦች)

| | | |
|---|---|---|
| " | " | ለምግብ መሸጫ |
| " | " | ለሽመና |
| " | " | ለንግድ (ኪዮስክ) |
| " | " | ለሸክላ ሥራ |
| " | " | ለብረታ ብረት ሥራ |
| " | " | ለጫማ ሥራና ጥገና |

በቤቱ ውስጥ የድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ባለቤቶች የማይኖሩበት ቢሆንና ነገር ግን ሠራተኞች የሚኖሩበት ከሆነ የቤት አገልግሎት ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት ይባላል።

ሐ. ሆቴል/ሆስቴል- በቆጠራው ቀን ቤቱ የሚያገለግለው በሆቴልነት ወይም በሆስቴልነት የሆነ እንደሆነ አገልግሎቱ ለሆቴል/ለሆስቴል ይባላል።

ሆቴል፣ የሚባለው 1. የምግብና የመኝታ ግልግሎት የሚሰጥ 2. የመጠጥና የመኝታ ግልጋሎት የሚሰጥ ወይም 3. የምግብ የመጠጥና የመኝታ ግልጋሎት የሚሰጥ ድርጅት ነው።

ሆስቴል፣ የሚባለው ብዙ ሰዎች ከመደበኛ ቤተሰብ እንዋንዋር ውጪ በአንድ ቤት ወይም ቤቶች በአንድነት እየኖሩ በቤትም ያሉትን መገልገያዎች ማለት ውኃን መብራትንና ሌሎች አገልግሎቶችን በጋራ ወይም በሕብረት የሚጠቀሙበትና በአንድ ድርጅት ሥር የሚተዳደርበት የጋርዮሽ መኖሪያ ሥፍራ ነው።

መ. ሌላ ጋርዮሽ፣ በቆጠራው ቀን ቤቱ የሚያገለግለው ለብዙ ሰዎች ሆኖ ሆቴል/ሆስቴል ካልሆነ ሌላ ጋርዮሽ ይባላል። ይህም ማለት በዝምድና ያልተሳሰሩና ከቤቱ በሚገኙ አገልግሎቶች በጋራ የሚጠቀሙ ሰዎች የሚኖሩበት ማለት ነው። እነዚህም:- ወህኒ ቤቶች አዳሪ ት/ቤቶች ሕጻናት ማሳደጊያዎች፣ ሆስፒታሎች የወታደር ካምፖች፣ ያረጁ ሰዎች መጦሪያዎች ፖሊስ ጣቢያዎች (እሥር ቤት ካላቸው)፣ የፀባይ ማረሚያዎች አድባራትና ገዳማት የሠራተኛ ካምፖች ... ወዘተ. ናቸው።

ሠ. ለድርጅት ብቻ:- በቆጠራው ቀን ቤቱ ሙሉ ለሙሉ ለድርጅት ሥራ ብቻ የሚያገለግል ከሆነ የቤቱ አገልግሎት ለድርጅት ብቻ ነው ተብሎ ይሞላል።

3. ስለ ቤቱ ግድግዳ፣ ጣሪያ ኮርኒስና ወለል

እያንዳንዱን ቤት አስመልክቶ ግድግዳው፣ ጣሪያውና ወለሉ በአብዛኛው ከምን እንደተሠራ የዕቃው ዓይነት ይጠየቃል። እንደዚሁም ቤቱ ኮርኒስ ካለው ኮርኒሱ በአብዛኛው ከምን እንደተሠራ ተጠይቆ መልሱ ይመዘገባል።

4. የቤቱ ይዞታ

በቆጠራው ወቅት የእያንዳንዱን የቤት ይዞታ የሚያመለክት መረጃ ይሰበሰባል። የቤት ይዞታ መረጃ የቤቱ ባለቤት ማን እንደሆነ የሚያመለክት መረጃ ነው። ቤቱ በነዋሪዎች ባለቤትነት፣ ከቀበሌ ተከራይተው በሚኖሩ ነዋሪዎች በመከራየት፣ ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ተከራይተው በሚኖሩ ነዋሪዎች፣ የኪራይ ልዩነት እየከፈሉ በሚኖሩ ነዋሪዎች፣ ከግለሰብ ተከራይተው በሚኖሩ ነዋሪዎች ወይም ከኪራይ ነፃ ሆነው በሚኖሩ ነዋሪዎች የተያዘ ሊሆን ይችላል። ስለዚህም ከእነዚህ የይዞታ ዓይነቶች ውስጥ ቤተሰቡ የሚኖርበት ቤት ይዞታ የትኛው እንደሆነ በመጠየቅ መረጃ ይሰበሰባል።

5. የቤት ኪራይ

ቤተሰቡ ከቀበሌ በመከራየት፣ ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት በመከራየት፣ የኪራይ ልዩነት በመክፈል እና ከግለሰብ በመከራየት የሚኖር ከሆነ በወር የሚከፈለው የኪራይ መጠን ስንት እንደሆነ ይጠየቃል። አንዳንድ ጊዜ አንድ ቤት ከአንድ ለበለጡ ቤተሰቦች የተከራየ ከሆነ የቤቱ የወር ኪራይ የሚባለው ሁሉም ቤተሰቦች የሚከፍሉት የወር ኪራይ ተደምሮ በአንድ ላይ ይሆናል። እንደዚሁም ቤተሰቡ የራሱ የሆነ ቤት እያለው ኪራዩ ከፍ ባለ በሌላ ቦታ የኪራይ ልዩነት እየከፈለ የሚኖር ከሆነ ለዚህ ቤተሰብ የኪራይ መጠን ተብሎ የሚወሰደው የሚከፈለው የኪራይ ልዩነት ነው።

ሐ. <u>የመኖሪያ ቤት መገልገያዎችና ክፍሎችን በተመለከተ፣</u>

አንድ የመኖሪያ ቤት እንደ ደረጃው ለነዋሪዎቹ አስፈላጊ ግልጋሎት የሚሰጡ ቁሳቁሶችና የቤቱ አካሎች ይኖሩታል። በዚህ ሥር ሊጠቀሱ የሚችሉ እንደ መብራት ቧንቧ ውኃ፣ መታጠቢያ ቤት ማዕድ ቤት፣ መጸዳጃ ቤት፣ ሬዲዮ፣ ቴሌፎን፣ ቴሌቪዥንና የተለያዩ ክፍሎች ይገኙበታል።

"ክፍል" ሲባል ዙሪያውን ከወለል እስከ ኮርኒሱ ወይም ጣራው ድረስ 2 ሜትር በሚደርስ ግድግዳ የተከበበና ቢያንስ አራት ካሬ ሜትር የሆነ ቦታ ሆኖ ስፋቱ ለአንድ አዋቂ ሰው አልጋ ለማዘርጋት የሚበቃ ሥፍራ ያለው ነው። ስለዚህ ጠቅላላ የቤቱ ክፍሎች የእንግዳ መቀበያ (ሳሎን)፣ የምግብ፣ የመኝታ፣ የወጥ ቤት፣ የሠራተኛ መኝታና ለሌላ ሥራ የሚያገለግሉ ክፍሎችንም ያጠቃልላል። ነገር ግን የመታጠቢያና የመጸዳጃ ክፍል የመተላለፊያ ኮሪደሮችንና በረንዳዎች እንደ ክፍል አይቆጠሩም።

1. <u>የመጠጥ ውኃ</u>

በቤቱ የሚኖሩ የቤተሰቡ አባላት ለመጠጥ የሚጠቀሙበትን ውኃ በአብዛኛው ከየት እንደሚያገኙ ይጠየቃል። የቤተሰቡ አባላት በአብዛኛው የመጠጥ ውኃ የሚያገኙት ከቧንቧ፣ ከተጠበቀ ጉድጓድ/ምንጭ፣ ካልተጠበቀ ጉድጓድ/ ምንጭ ወይም ከወንዝ፣ ሐይቅ/ኩሬ ሊሆን ይችላል። የቤቱ ነዋሪዎች የመጠጥ ውኃ የሚያገኙት ከተጠበቀ ጉድጓድ/ምንጭ ነው የሚባለው ውኃውን ሊበክሉ ከሚችሉ ነገሮች ራቅ ብሎ የተዘጋጀ፣ ዙሪያው በሲሚንቶ ተገንብቶ ከሲሚንቶ ወይም ከሌላ የዕቃ ዓይነት የተሰራ ጥብቅ ክዳን ካለው ጉድጓድ/ምንጭ የሚጠቀሙ ሲሆን ነው።

2. <u>ማድቤት</u>

ቤቱ ለምግብ ማብሰያ የሚጠቀምበት የተለየ ክፍል/ማድቤት ያለው መሆኑና አለመሆኑ ይጠየቃል። ቤቱ ማድቤት የለውም የሚባለው የቤተሰቡ አባላት የምግብ ማብሰያ ቦታ የሌላቸው በመሆኑ የቤተሰቡ አባላት በሚያድሩበት ክፍል ወይም ከብቶች በሚያድሩበት ክፍል ውስጥ ወይም ከቤት ውጭ በሜዳ፣ በዛፍ ጥላ ሥር...ወዘተ. ምግብ የሚያበስሉ ሲሆን ነው። በተጨማሪም የምግብ ማብሰያ ክፍል ያላቸው ግን ምግብ የማያበስሉ ቤተሰቦች ቢያጋጥሙ የሚኖሩበት ቤት ማድቤት እንደሌለው ይቆጠራል።

በአንፃሩም ማድቤት ላለው ቤት ያለው የማድቤት ሁኔታም ይጠየቃል። የተለያዩ የማድቤት ሁኔታ የሚባሉት ቤቱ ለማድቤትነት ብቻ የሚያገለግል ክፍል ያለው መሆኑን ሰዎች የሚያድሩበት ቤት እንደማድቤት ይጠቀሙበት መሆኑን እንዲሁም ከብቶች የሚያድሩበትን ክፍል እንደማድቤት የሚጠቀሙበት መሆኑን የሚያሳይ ነው።

3. <u>ማገዶ</u>

የቤቱ ነዋሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ለምግብ ማብሰያ ስለሚጠቀሙት የማገዶ ዓይነት የሚያሳይ መረጃ በቆጠራው ወቅት ይሰበሰባል። አንዳንድ ቤተሰብ ምግብ የማያበስሉ ለምሳሌ:- ሆቴል የሚመገቡ፣ ከሌላ ቦታ የሚመገቡ .... ወዘተ. በመሆናቸው ማገዶ የማይጠቀሙ ቢሆንም አብዛኛው ቤተሰብ ግን ኬሮሲን/ነጭ ጋዝ፣ ከሰል፣ እንጨት፣ ቅጠል፣ ኩበትና የመሳሰሉትን

ወይም አንዱና ሌላውን በማጣመር ለምግብ ማብሰያነት ሊጠቀም ስለሚችል አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀመው የማገዶ ዓይነት የትኛው እንደሆነ ተለይቶ ይመዘገባል።

4. <u>የመፀዳጃ ቤት</u>

ቤቱ የመፀዳጃ ቤት እንዳለውና እንደሌለው ይጠየቃል። ቤቱ የመፀዳጃ ቤት ካለው የመፀዳጃ ቤቱ ዓይነት በዉኃ የሚወርድ ወይም ደረቅ ጉድጓድ ሊሆን ስለሚችል የትኛው ዓይነት እንደሆነ በመለየት ይመዘገባል። ነገር ግን የመፀዳጃ ቤቱ በመበላሸቱ/በመፍረሱ ወይም በመሙላቱ የተነሳ ጥቅም የማይሰጥ ከሆነና ይህም ሊጠገን የማይችል ከሆነ ቤቱ መፀዳጃ ቤት እንደሌለው ይቆጠራል።

5. <u>የገላ መታጠቢያ</u>

እያንዳንዳቸው በከተማ የሚገኙ ቤቶች የገላ መታጠቢያ እንዳላቸውና እንደሌላቸው በመጠየቅ መረጃ ይሰበሰባል። የገላ መታጠቢያ ቤት ላላቸው ደግሞ ያላቸው የገላ መታጠቢያ ዓይነት የገንዳ ወይም የሻወር መሆኑ ይጠየቃል።

6. <u>መብራት</u>

እያንዳንዱ የከተማ ቤት መብራት እንዳለውና እንደሌለው ይጠየቃል። መብራት ላላቸው ቤቶች ደግሞ በተጨማሪ ያላቸው መብራት ኤሌክትሪክ፣ ፋኖስ፣ ኩራዝ ወይም ሌላ ዓይነት መሆኑ ተጣርቶ መረጃ ይሰበሰባል።

7. <u>ሬዲዮና ቴሌቪዥን</u>

በቆጠራው ወቅት በእያንዳንዱ ቤት ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን መኖር አለመኖሩ ይጠየቃል። ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን በቤቱ ውስጥ ኖሮ በቆጠራው ወቅት በመበላሸት ምክንያት የማይሰራም ቢሆን ቤተሰቡ ወደፊት የሚያስጠግኑት ከሆነ በቤቱ ውስጥ ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን እንዳለ ይቆጠራል።

ቤቱ ከአንድ በበለጡ ቤተሰቦች የተያዘ ከሆነ በቤቱ ውስጥ ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን አለ የሚባለው ቢያንስ በቤቱ ውስጥ ከሚኖሩት ቤተሰቦች አንዱ ሲኖረው ነው።

8. <u>ቴሌፎን</u>

በቆጠራው ወቅት በከተማ የሚገኙ ቤቶች ቴሌፎን እንዳላቸውና እንደሌላቸው ይጠየቃል። በቤቱ ውስጥ ቴሌፎን ኖሮ በቆጠራው ወቅት በመበላሸት ምክንያት የማይሰራ ቢሆንም ወደፊት የሚጠገን ከሆነ በቤቱ ውስጥ ቴሌፎን እንዳለ ይቆጠራል።

## 7. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈጸሚያ አዋጅና የግለሰቦችና ድርጅቶች ኃላፊነትና ግዴታ

### 7.1 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈጸሚያ አዋጅ

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት የሕብረተሰቡን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ለማሻሻል ለሚደረገው የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማት ፕላን ዝግጅት አስፈላጊ ስለሆነና የቆጠራው ሥራ ብሄራዊና በአፈጻጸሙም ሰፊት ያለውና ውስብስብ ስለሆነ ለዚሁ ተግባር አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የሕዝብና ቤት ቆጠራ አዋጅ ቁጥር 32/1985 ዓ.ም ታውጅዋል። አዋጁ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ቆጠራውን በሚመለከት አስፈላጊውን ድጋፍና ትብብር እንዲያደርጉ፣ ኅብረተሰቡ ትክክለኛውን መረጃ እንዲሰጥ እንዲሁም በቆጠራው ሥራ የሚሳተፉት ሁሉ ሥራቸውን ጥራት ባለው ሁኔታ የማከናወን ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ያረጋግጣል።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን የተጣለበትን ኃላፊነትና ተግባር ለመወጣት አመች በሚሆንበት መንገድ ከብሄራዊ አንስቶ እስከ ወረዳ ድረስ በኮሚቴዎችና በጽሕፈት ቤቶች ተዋቅሮአል። ኮሚቴዎች አብዛኛውን ጊዜ አመራር የመስጠትና እንደ አስፈላጊነቱ የፖሊሲ እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን በተጨማሪ ስለ ቆጠራው ክንውን የቅርብ ክትትል ያደርጋሉ። ጽሕፈት ቤቶች ግን በይበልጥ ኃላፊነታቸው ቆጠራውን ማስፈጸም ይሆናል። የቆጠራው ኮሚሽን በየደረጃው መከናወን የሚገባቸውን ተግባሮች በመለየትና የአፈጻጸም ቅደም ተከተል በማውጣት የቆጠራው ሥራ በማይተጓጎል ሁኔታ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል። ለቆጠራው የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራ አስፈላጊነት ታምኖበት ከብሄራዊ ደረጃ እስከ ወረዳ ድረስ የኮሚሽኑ አንዱ አካል በመሆን የትምህርትና ቅስቀሳ ኮሚቴ ተዋቅሮአል። የትምህርትና የቅስቀሳው ሥራ አፈጻጸም በየደረጃው ከበላይ አካል በሚተላለፍ መመሪያ መሠረት ይሆናል።

በአዋጁ ውስጥ እንደተደነገገው ቆጠራውን በሚመለከት የሚከተሉት ግዴታዎች ተገልጸዋል።

ሀ. ማንኛውም መንግሥታዊ ወይም ሕዝባዊ ድርጅት ወይም ግለሰብ ለሚከናወነው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ የመተባበር ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣

ለ. በቆጠራው ጊዜ መረጃ እንዲሰጥ የተጠየቀ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ከኮሚሽኑ የተሰጠውን መታወቂያ ለሚያሳይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ሰብሳቢ ወይም ተቆጣጣሪ ትክክለኛውን መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣

ሐ. ማንኛውም የቤት ወይም የቅጥር ግቢ ባለንብረት ወይም ባለይዞታ ከኮሚሽኑ የተሰጠውን መታወቂያ ለሚያሳይ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ሰብሳቢ ወይም ተቆጣጣሪ ወደ ተባለው ንብረት እንዲገባ የመፍቀድ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ናቸው።

ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ፣ ይሽንን በሚመለከት ሐሰተኛ መረጃ የሰጠ ወይም በማንኛውም የቤት ወይም የቅጥር ግቢ ባለንብረት ገብቶ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ለማግኘት ምርመራ እንዳይደረግ ያሰናከለ፣ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ከአምስት መቶ ብር ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ እስራት፣ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሲሆን ከ2000 ብር (ከሁለት ሺህ ብር) በማይበልጥ መቀጫ የሚቀጣ መሆኑን አዋጁ ያብራራል።

## 7.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ በሚከናወንበት ወቅት ግለሰቦችና ድርጅቶች ስለ ሚኖራቸው ኃላፊነትና ግዴታ

ቆጠራው የታለመለትን ግብ መታ የሚባለው በታቀደው ጊዜ ውስጥ የሚፈለጉትን መረጃዎች በተሟላና ትክክል በሆነ አኳኋን ለመሰብሰብ ሲቻል ነው። በዚህ አኳያ ግለሰቦችና ድርጅቶች ታላቅ አስተዋጽኦ ይጠበቅባቸዋል። ሁኔታውን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ግለሰቦችና ድርጅቶች ከቆጠራው ሥራ አንጻር የሚኖራቸውን ኃላፊነትና ግዴታ በሚከተለው አኳኋን ለማየት ይቻላል።

### 7.2.1 ግለሰቦችን በሚመለከት፥

ሀ. በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን በየደረጃው በተቋቋመው ድርጅታዊ መዋቅር የተመደቡት ሠራተኞችና የሠራተኞች ኃላፊዎች የተጣለባቸውን ኃላፊነትና ተግባር ለመወጣት መመሪያን በመከተል በወቅቱ ጥራት በተሞላውና ባላሰለሰ ጥረት ሥራቸውን የማከናወን ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።

ለ. ቆጠራው ለሀገር ልማትና ደህንነት የሚያደርገውን ታላቅ አስተዋጽኦ በማጤን ግለሰቦች ቆጠራው በሚካሄድበት ጊዜ ለሚጠየቁት የመረጃዎች ዓይነት ሁሉ የተሟላና ትክክለኛ መረጃ የመስጠት ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።

ሐ. ለቆጠራው ሥራ ከነውን ለሚጠየቁት ሌሎች ድጋፍና ትብብር ግለሰቦች ተፈላጊውን ሁሉ የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።

### 7.2.2 ድርጅቶችን በሚመለከት፥

ሀ. በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን መዋቅር በየደረጃው ተመድበው የሚሠሩ የድርጅቶች ሠራተኞችና ኃላፊዎች የተጣለባቸውን ኃላፊነትና ተግባር ለመወጣት መመሪያን በመከተል፥ ቆጠራው የሚጠይቀውን ሁሉ የማሟላት ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።

ለ. እንደ አስፈላጊነቱ በቆጠራው ገዜ ለሚጠየቁት ሁሉ ድርጅቶች የተሟላና ትክክለኛ መረጃ የመስጠት ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።

ሐ. ቆጠራው በሚካሄድበት ወቅት የሚመለከታቸው ድርጅቶች የቆጠራውን ሠራተኞች፥ ዶኩሜንቶችና ሌሎች ማተሪያሎች በማጓጓዝ ረገድ ቅድሚያና አስፈላጊውን ሁሉ የማድረግ፥ ለቆጣሪዎችና ለተቆጣጣሪዎች ጊዜያዊ መጠለያ እንዲያገኙ የማድረግ፥ በተለይ በመጠነኛ ወጪ ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች ምግብ እንዲያገኙ የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።

## 8. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ድርጅታዊ መዋቅር ተግባርና ኃላፊነት

የሕዝብና ቤት ቆጠራ በጣም ከፍተኛ የሆነ ብሄራዊ የመረጃ መሰብሰብ ሥራ ከመሆኑም በላይ በአፈጻጸሙ መላ የአገሪቱን ነዋሪዎች ትክክለኛ መረጃ እንዲሰጡ ማሳመንና የተለያዩ የሕዝብና የመንግሥት አካላትን በማንቀሳቀስ ለሥራው ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ማደራጀትና ማስተባበርን የሚጠይቅ ውስብስብ ተግባር ስለሆነ ለዚሁ ተግባር የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈጸሚያ አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ የሽግግሩ መንግሥት

እንደ መጀመሪያው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ሁሉ የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ኮሚሽንን በአዋጅ ቁጥር 32/1985 ዓ.ም አቋቁሟል።

በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን የበላይ አመራርና የፖሊሲ ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን ተጠሪነቱ ለተወካዮች ምክር ቤት ነው። የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 8/1980 ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት በተጨማሪ የሕዝብና ቤት ቆጠራን ለማስፈጸም በወጣው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 32/1985 የተሰጠውን ተጨማሪ ተግባርና ኃላፊነት ያከናውናል። በዚሁ መሠረት ባለሥልጣኑ ያለው የሰው ኃይል፥ ማቴሪያልና ፋይናንስ ለቆጠራው ተግባር ይውላል። የማእከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በማዕከልና በ14 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተዋቀረ ሲሆን በዋና ሥራ አስኪያጅ፥ በሁለት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጆችና በሕዝብ ጥናት ማዕከል ኃላፊ ይመራል። መ/ቤቱ በአጠቃላይ ከ 1,600 በላይ ቋሚና የኮንትራት ሠራተኞች አሉት።

ከላይ እንደተገለጸው በማዕከል፥ በብሄራዊ ክልል በዞንና በወረዳ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን የተቋቋመ ሲሆን የማዕከሉ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ የኮሚሽኑም አባላት የሚከተሉት ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ጠቅላይ ሚኒስትር........................... | ሰብሳቢ |
| 2. | የፕላንና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ............ | አባልና ምክትል ሰብሳቢ |
| 3. | የማስታወቂያ ሚኒስትር........................ | አባል |
| 4. | የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ................ | " |
| 5. | የገንዘብ ሚኒስትር ........................ | " |
| 6. | የግብርና፥ የአካባቢ ጥበቃና ልማት ሚኒስትር ........ | " |
| 7. | የትምህርት ሚኒስትር ....................... | " |
| 8. | የውጭ ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር ............ | " |
| 9. | የክልል ጉዳይ ዘርፍ ኃላፊ .................... | " |
| 10. | የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ............... | አባልና ፀሐፊ |

በብሄራዊ ክልል በዞንና በወረዳ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ሰብሳቢዎች የመስተዳድር ሥራ አስፈጻሚ ሊቃንመናብርት ሲሆኑ አባላቱም በማዕከላዊ ኮሚሽን ተወስነዋል።

8.1 <u>የማዕከላዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር</u>:-

ሀ. የቆጠራ ካርታ ሥራና የሕዝብና ቤት ቆጠራን በሚመለከት የፖሊሲ መመሪያ ማውጣትና አፈጻጸማቸውን መከታተል፥

ለ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማስፈጸሚያ ካርታና ቆጠራው የሚከናወንበትን ጊዜና የሚሰበሰበው የመረጃ ዓይነት መወሰን፥

ሐ. ስለቆጠራ ካርታ ሥራና ስለሕዝብና ቤት ቆጠራ ሁኔታ ለሕዝብ ማስታወቅ፥

መ. ከብሄራዊ ክልል ኮሚሽን በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ መስጠት ናቸው።

8.2 ከማዕከላዊ ኮሚሽን በታች እስከ ወረዳ የሚገኙ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽኖች ሥልጣንና ተግባር:-

ሀ. ከማዕከላዊ ኮሚሽኑ የተላለፉ መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣

ለ. ለቆጠራ ካርታ ሥራና ለሕዝብና ቤት ቆጠራ አፈጻጸም በክልላቸው ውስጥ የሚገኙውን ሕዝብ እንዲሁም መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶችን መቀስቀስና ማስተባበር፣

ሐ. የክልላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ ለቆጠራ ካርታ ሥራና ለሕዝብና ቤት ቆጠራ አፈጻጸም ስልቶችን መቀየስ፣

መ. ከበላይ ኮሚሽን የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ማከናወን ናቸው።

## 9. የሕዝብና ቤት ቆጠራ የመስክ ሥራ ሂደት

ለሚካሄደው የሕዝብና የቤት ቆጠራ አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ሲባል አገሪቷን በአብዛኛው አካባቢ በቆጠራና በመቆጣጠሪያ ቦታዎች በመሸንሸን ካርታዎች እንዲዘጋጁ ተደርጓል። የቆጠራ ካርታ ሥራው መሠረት ያደረገው በገጠር የገበሬ ማህበራትን/ዝቅተኛ የአስተዳደር ክልሎችን በከተማ የቀበሌ ማኅበራትን ሲሆን የቆጠራ ቦታ አሸናሸኑ ከ150-200 ቤተሰቦች እንዲይዝ ተደርጎ ነው። በዚህ መሠረት በገበሬ ማህበርና በቀበሌው እንደሚኖረው የቤተሰብ ብዛት እያንዳንዱ የገበሬ ማኅበር ወይም ቀበሌ አንድ ወይም ከአንድ የበለጠ የቆጠራ ቦታ ሊኖረው ይችላል። ለተደረገው ሽንሸና ወሰኑን ወይም ክልሉን ለመለየት በሚያስችል አኳኋን ካርታ ተዘጋጅቷል። ከዚያም አንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ በአማካይ አምስት የቆጠራ ቦታዎች በሚያካልል ሁኔታ የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ ተዘጋጅቷል። የተዘጋጀውን ካርታ በመጠቀም የቆጠራው የመስክ ሥራ ይካሄዳል።

የቆጠራው የመስክ ሥራ በእያንዳንዱ የቆጠራ ቦታ ውስጥ ከሚገኙትና ከሚመለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች በቆጠራው ተፈላጊ የሆኑት መረጃዎች የሚሰበሰቡበት የተግባር ክንውን ነው። የቆጠራው የመስክ ሥራ ሁለት አበይት የአሠራር ሂደት ይኖሩታል እነርሱም:-

ሀ. የቤቶችና የቤተሰቦች ምዝገባ ማካሄድ

ለ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ መጠይቆች መሙላት

የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅቶች ምዝገባ የቆጠራው የመስክ ሥራ መጀመሪያ ይሆናል። ምዝገባው የሚካሄደው በቆጣሪዎች አማካኝነት ሆኖ በየቆጠራው ቦታ ውስጥ ሥርዓት በአለው መልክ ከቤት ቤት በመዘዋወርና የሚመለከታቸውን የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅት ኃላፊዎች በማነጋገር ነው። በቆጠራው ጊዜ ቤቶች በሚሰጡት አገልግሎት ዓይነት ማለትም ለመኖሪያ ብቻ የሚያገለግሉ፣ ከፊል ለመኖሪያ ከፊል ለድርጅት የሚያገለግሉ፣ ለድርጅት ብቻ የሚያገለግሉ፣ ለጋርዮሽ መኖሪያ የሚያገለግሉ እንዲሁም ያልተያዙ ወይም በመሠራት ላይ ያሉ ቤቶች ሁሉ እንደየሁኔታው ይመዘገባሉ። በተጨማሪ ቤቶች የሚሰጡት አገልግሎት ከፊል ለመኖሪያ ከፊል ለድርጅት ወይም ለድርጅት ብቻ ከሆነ ድርጅቶቹ የሚያመርቱት ዋና የምርት ወይም የንግድ ዓይነት ወይም የሚሰጡት ዋና የአገልግሎት ዓይነት እንዲሁ ይመዘገባል። በምዝገባው ጊዜ በድርጅቶች ውስጥ ስለሚሠሩት ቋሚ ሠራተኞች ብዛት መረጃዎች ይሰበሰባሉ። እንዲሁም በግብርና ለተሰማሩ ቤተሰቦች የሚያመርቱት የግብርና ዓይነት ይመዘገባል።

በእያንዳንዱ የቆጠራ ቦታ የሚከናወነው ምዝገባ በቦታው ውስጥ የሚገኙትን የቤቶች፣ የቤተሰቦችና የድርጅቶች ብዛት ለማወቅና ቆጠራው በሚካሄድበት ወቅት ቤቶችና ቤተሰቦች ሳይዘለሉ ወይም ሳይደጋገሙ በተሟላ አኳኋን መቆጠራቸውን ለመቆጣጠር እንዲረዳ ነው። በተጨማሪም ምዝገባው ወደፊት የኢኮኖሚና የሶሻል ጥናቶች ለማካሄድ መሠረታዊ መረጃዎች ያስገኛል።

በእያንዳንዱ ቆጠራ ቦታ ውስጥ የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅት ምዝገባ እንደተጠናቀቀ ልክ ምዝገባው በተከናወነበት አኳኋን ቆጣሪዎች ሥርዓት በአለው መልክ ከቤት ቤት በመዘዋወርና የሚመለከታቸውን የቤተሰብና የድርጅት ኃላፊዎች በማነጋገር በቆጠራው ቦታ ውስጥ ለሚኖሩት ሁሉ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ መጠይቆች ይሞላሉ። አብዛኛውን ጊዜ በዚህ ዓይነት ሥርዓት መጠይቆች የሚሞሉ ሲሆን መኖሪያ ቤት ለሌላቸው ግን መጠይቆቹ የሚሞሉት በሚያድሩበት ቦታ ነው። የሕዝብና ቤት ቆጠራ መጠይቅ በሚሞላበት ጊዜ ሕፃን፣ ሽማግሌ፣ ታሞ የተኛ ...ወዘተ. ሳይተው ሙሉ በሙሉ እንዲቆጠሩና አንድ ጊዜ የተቆጠሩት ደግሞ ተደግመው እንዳይቆጠሩ የማድረግ ኃላፊነት የሚመለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ስለሆነ ይኸንኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች አስቀድመው እንዲያውቁት ያስፈልጋል።

የቆጠራው የመስክ ሥራ የሚካሄደው በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን በሚወስነው የቆጠራ ቀን ሲሆን ግለሰቦችና ድርጅቶች የቆጠራውን ቀን እንዲገነዘቡና እራሳቸውንም ለቆጠራው አዘጋጅተው እንዲቆዩ የቆጠራውን ቀን ኅብረተሰቡ በቅድሚያ እንዲያውቀው ማድረግ ተገቢ ነው። የቆጠራውም ቀን ታስቦ እንዲውል ይጠበቃል።

የቆጠራውን የመስክ ሥራ ለማከናወን ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች ቤት ከቤት በሚዘዋወሩበት ጊዜ የቆጠራ ባጅና የመታወቂያ ካርድ ይዘው እንዲዘዋወሩ ይደረጋል። ይኸም የቆጠራ ሠራተኞች መሆናቸውን ከማረጋገጡም በላይ ሕዝቡ ያላንዳች ጥርጣሬና ፍርሀት አስፈላጊውን ትብብርና ድጋፍ እንዲያበረክት ይረዳል።